# የፃራ ብሔረሰብ ትውፊታዊ እምነት

ፍሬሕይወት ባዩ[1]

**አጽኀሮተ ጽሁፍ**

የፃራ ብሄረሰብ በደቡብ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት በካፋ ዞን ከሚገኙ ሶስት ብሄረሰቦች መካከል አንዱ ነው። የጥናቱ ዋና አላማ የፃራን ብሄረሰብ ትውፊታዊ እምነት ጽንሰ ሀሳብ፤ የእምነቱ መሪ እና አማኞቹ በየእለት ህይወታቸው የሚተገብሯቸውን ክዋኔዎች መተንተን ነው። ጥናቱ በዋናነት የሚመልሰው ጥያቄ የፃራ ብሄረሰብ ትውፊታዊ እምነት ክዋኔዎች ምን ምንድን ናቸው? የሚል ነው። የጥናቱ የመረጃ ምንጭ በመስክ ጥናት የተገኘ ቀዳማይ መረጃ ሲሆን መረጃው የተሰበሰበው በቃለመጠይቅ በምልከታና በቡድን ውይይት ነው። የፃራ ብሄረሰብ በጥቅሉ እንደ ግለሰብ እንደ ቤተሰብ እንደማህበረሰብ ትውፊታዊ እምነቱን በተለያዩ የህይወት መልኮች ውስጥ ይከውናቸዋል። በዚህ ጥናት ኤቃ የእምነቱ መሪ ሲሆን የተሾመው በፈጠረው የሪዶንቲ ነው። ህዝቡም የሪዶንቲ ያዘዘውን አምኖ፣ አክብሮና ታዞ ይኖራል። የፃራ ብሄረሰብ የጎሳ ብዛት ከሰላሳ በላይ ሲሆን እያንዳንዱ ጎሳ የየራሱ ኤቃ አለው። በደን ውስጥ የሚኖር ቆሉ የተባለው መንፈስ እሸት እህል በየአመቱ ይሰጠዋል። ቆሉ አይታይም ተለይተው በሚታወቁ ደኖች ውስጥ ይኖራል። ቆሉ ያለበት ደን የመንፈሱ ማረፊያ ስለሆነ አይቆረጥም አይመነጠርም። ከኤቀትሳ ጎን ለጎን ለሰዎች ችግር እንዲፈቱ ስጦታ የተሰጣቸው ግለሰቦችም ገራትሳ፣ ቡርገትሳ፣ ከራትሳ እና ገራ የሚባሉ ውሃ አፍሶ በማየት፣ የጎሽ ቆዳ ቁራጭ በመምታት፣ የአብት አንጀት በማንበብ የሰዎችን ችግር ይፈታሉ።

**ቁልፍ ቃላት**: [የፃራ ብሄረሰብ፣ ትውፊታዊ እምነት፣ የሪዶንቲ፣ ኤቃ፣ ቆሉ]

## 1. መግቢያ

ይህ ጥናት የሚመለከተው የፃራ ብሄር የሚያምንበትን ኤቃ የሚባለውን ትውፊታዊ እምነት ነው። የፃራ ብሄር በደቡብ ብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦች ክልላዊ መንግስት በካፋ ዞን በተለይም በጎባ ወረዳ ይገኛል። የካፋ ዞን አስረሀንድ ወረዳዎችና አንድ ከተማ አስተዳደር ያለው ሲሆን በ309 የገጠር እና 16 የከተማ ቀበሌዎች አሉት፡፡ ካፋ ዞኑ በሰሜን፣ በሰሜን ምስራቅና በሰሜን ምዕራብ ኦሮሚያ ክልላዊ መንግስት ከጅማ ዞን፣ በምስራቅና በደቡብ ምስራቅ ከኮንታ ልዩ ወረዳ፣ በደቡብ ከደቡብ ኦሞ ዞን፣ በደቡብ ምዕራብ ከቤንች ማጂ ዞንና በምዕራብ ከሸካ ዞን ይዋሰናል፡፡

በካፋ ዞን ካፊቾ፣ ናኢና የፃራ ብሄረሰቦች ይገኛሉ። ጎባ ወረዳ የፃራ ብሔረሰብ በብዛት የሚገኝበት ሲሆን ሆኖም በአጎራባቾቹ ኮንታ ልዩ ወረዳ እና በሌሎቹም ተሰባጥረው ይኖራሉ። የፃራ ብሄረሰብ አጠቃላይ የህዝብ ብዛት በ1998ዓ.ም የህዝብና ቤት ቆጠራ መረጃ መሰረት 13,210 እንደሆን ይገልጻል። ፃራ በሰሜን የካፊቾ ብሄረሰብ፣ በሰሜናዊ ምእራብ የናኢ ብሄረሰብ፣ በሰሜን የኮንታ

[1] አዲስ አበባ ዩንቨርሲቲ የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ባህሎች አካዳሚ የፎክሎር ተመራማሪ።

ልዩ ወረዳ፣ በምስራቅ፣ በደቡብ ምስራቅ እና በደቡብ እንዲሁም በደቡብ ምእራብ የሚኢኤት ብሄረሰብ ያዋስኑታል (የብሄረሰቦች ምክር ቤት ፕሮፋይል፣ 2002)።

የተለያዩ ጽሁፎች ላይ እንዲሆም በአካባቢው በሚገኙ አጎራባች ህዝቦች ሲጠራቸው "ጫራ" በማለት ነው። ሆኖም ህዝቡ እራሱን የሚጠራ ፃራ ብሎ ነው። ፃራ የህዝቡ መጠሪያ፣ ጻሪ የሚኖሩበት ምድር ወይም ቦታ ስም ሲሆን ቋንቋቸውን ደግሞ ጻረትሰ ኖና በማለት ይጠሩታል። የህዝቡን ሃይማኖት ስንመለከት ባህላዊው የኤቃ እምነት ተከታይ ሲሆኑ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶና የፕሮቴስታንት የካቶሊክ ሃይማኖት ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በመስፋፋት ላይ ይገኛል።የፃራ ህዝብ በከፊል በአርብቶ አደር በከፊል በእርሻ ስራ ይተዳደራል።

"ፎክእምነት" ("folk-belief") Degh (1972) እንደምታስረዳው 'ትውፊታዊ (traditional) እምነት' ተብሎም ይጠቀሳል፡፡ ፎክ እምነት በመርህ ደረጃ 'ትልልቅ' ተብለው የሚጠቀሱትን፣ ለምሳሌ፡-የክርስትና፣ የአይሁድ፣ የእስልምና፣ የቡድሀ፣ ወዘተ፣ ሃይማኖቶች እምነቶችንም ጨምሮ የሚይዝ ፅንሰ-ሀሳብ ነው፡፡ Motz (1998:340) እንደሚለው ደግሞ "የእምነት ሥርዓት የፎክሎር ጥናት ቁልፍ ፅንሰ-ሀሳብ ነው። የእምነት ሥርዓትን ሳይጨምር ስለፎክሎር መነጋገር አስቸጋሪ ይሆናል፡፡ በአንድ 'ፎክ' ወይም ማህበራዊ ቡድን አመለካከቶች ላይ ተፅዕኖ ማድረጋቸው ብቻ ሳይሆን በእነሱም ላይ የነበረው የማህበራዊ ቡድኑ አስተሳሰብ ተፅዕኖ እንደሚያደርግባቸው Mullen (2000) ያስረዳል፡፡ በመቀጠልም "እንደ አንድ የፎክሎር ዓይነት (genre) እምነት ... ርዕይዮተ-ዓለምን፣ ሥነ-ኀላዌን (cosmological)፣ የሰማያውይውንና የምድራዊውን አፈጣጠር፣ መንፈሳዊ እምነቶችን፣ ወዘተ፣ ሁሉ የሚያካትት ሰፊ ፅንሰ-ሀሳብ ነው።" ጠበብ አድርገን እንውሰድ ብንል እንኳዋን መለኮታዊ ኀይልን፣ ባዕድ-አምልኮን፣ መናፍስትን፣ መተትን፣ ድግምትን፣ ልማዳዊድርጊቶችን፣ ሥርዓተ-በዐላትን፣ ገድሎችን፣ ተአምራትን፣ ሙዋርትን፣ ባህላዊህክምናን፣ እናየመሳሰሉትን ያጠቃልላል። እምነት የአንድ 'ፎክ' ወይም ቡድን ቁልፍ የመገለጫ ፅንሰ-ሀሳብ ሲሆን ረቂቅ የሆነ የእውቀት ደረጃነው፡፡ ስለዚህ ለምርምር (ለጥናት) ተግባር ጠቃሚ የሆኑ የፎክሎር ዓይነቶች በመሆናቸው ተጨባጭ ድርጊቶችንና ባህላዊ መገለጫዎችን መመልከት አለብን በማለት ያስረዳል (Mullen 2000፡ 120-122)፡፡

የትውፊታዊ እምነት ጥናት የአንድን ህዝብ በተለያየ ደረጃ ላይ የሚገኙ የማህበረሰብ ክፍሎችን ሁሉ የሚያካትት ነው (Anders 2012: 9)። ከትውፊታዊ እምነት መገለጫዎች መካከል አንዱ የተጻፈ ደንብና መመሪያ አለመኖር ነው። የእምነቱ ደንብ እና መመሪያ በቃል ከትውልድ ወደ ትውልድ የሚተላለፍ ነው። በተለይም የአፍሪካን ትውፊታዊ እምነት አስመልክቶ ካጠኑና ጠባዩን ከዘረዘሩት መካከል Awolalu (1976: 2) ትውፊታዊ እምነት በወረቀት ላይ የሰፈረ ሳይሆን በአማኙ ልብ ውስጥ የተጻፈ እና በቃል ታሪኩ በተለያዩ ከዋኔዎች በእምነታዊ ጉዞ አማካይነት የሚተላለፍ እንደሆነ ገልጿል።

በሀገራችን በእስልምና እና በክርስትና ላይ የተጠናውን ያህል በትውፊታዊ እምነት ላይ የተጠና ጥናት የለም ለማለት ይቻላል። ሆኖም ሌሎች ርእሰ ጉዳዮችን አንስተው እግረመንገድ የተለያዩ

ትውፊታዊ እምነቶች እንዳሉ የሚጠቁሙ ጥናቶች አሉ። ትውፊታዊ እምነትን በተመለከተ ከተጠኑ ጥናቶች መካከል አንዱ ወርቅነህ ቀልቤሳ(2015) እና ሌሎችም የኦሮሞ  የዋቄፈና ትውፊታዊ እምነት ላይ ከሌላው በተሻለ ተጠንቷልው። የዋቄፈና ሃይማኖት፣ የዋቄፈና እምነት እያሉ በተለዋዋጭ ይጠቀሙበታል።

> እምነት (faith)፤ አመንታ = እምነት (belief) የሚለ ትርጉሞችን ይይዚል፡ ፡ በኦሮሚኛ በሚጻፊ ስነ-ጽሁፍች ውስጥ ግን እንደ ጸሃፊዎቹ አረዳድ ሦስቱም እየተለዋወጡ ሃይማኖትን በመግለጽ ጥቅም ላይ ሲውሉ ይታያሉ፡፡ ይህ የሆነው የዋቄፈናን ጽንሰ ሀሳቦች በተለያዩ እይታዎች ከመረዳት የተነሳ ይመስላል፡፡ በኦሮሚኛ በሚጻፉ ስነ-ጽሁፍች ውስጥ ግን በእነዚህ ጸሃፊዎች አረዳድ ሦስቱንም እየለዋወጡ ሃይማኖትን ለመግለጽ ጥቅም ላይ ሲውሉ  ይታያሉ፡፡ ይህ የሆነው የዋቄፈናን ጽንሰ ሀሳቦች በተለያዩ  እይታዎች ከመረዳት የተነሳ ይመስላል (ቀነአ፣ 2010 89)፡፡

ትውፊታዊ እምነት፣ ሃይማኖት እንዲሁም ሌሎች ተያያዥ ቃላት ለአንድ ጽንሰ ሀሳብ በተለዋዋጭነት ይውላሉ። በዚህ ጥናት ትውፊታዊ እምነት የሚለው ተመርጧል። በዚሁ መሰረት ከዚህ ጥናት ጋር የቀረበ ዝምድና ያለው ቀደምት ጥናት በኦሮሞ የዋቄፈና ሃይማኖት ላይ የተጠናው ጥናት ነው።

ለዚህ ጥናት መጠናት ሰበብ የሆነው የተቀናጀ የምርምር ፕሮጀክት[2] ሲሆን በተቀናጀ የምርምር ፕሮጀክት ይጠና የነበረው ርእሰ ጉዳይ የፃራ ብሄረሰብ ቃላዊ ትርክቶች እና ቁሳዊ ባህል ነው። ሆኖም ጥናቱ ሲካሄድ የፃራ ብሄር ተወላጅ የሆኑት መረጃ አቀባዮች ቃላዊ ትረካዎችንና ቁሳዊ ባህልን በተመለከተ ጥያቄ ሲጠየቁ በተለያየ መልኩ ትውፊታዊ እምነታቸውን የሚመለከቱ መረጃዎች አያይዘው ያነሱ ነበር። ስለ ትውፊታዊ እምነት የሚያነሷቸው መረጃዎችም በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ከሚጠናው ቃላዊ ትረካዎችም ሆነ ከቁሳዊ ባህላቸው ጋር የተያያዘ ነው። ስለዚህ ለሚጠናው ጥናት ግብአት የሚሆን የፃራን ብሄር ትውፊታዊ እምነት በተመለከተ የተጠና ቀደምት ጥናት ባለመኖሩ ስለእምነታቸው ሳያውቁ ሌላውን ማጥናት የሚያጎላቸው በርካታ ሀሳቦች ይኖራሉ በሚል እሳቤ ይህን ጥናት ለማጥናት መነሻ ምክንያት ሆኗል።

---

[2] ከ2009 እስከ 2011 ዓ.ም በአዲስ አበባ ዩንቨርሲቲ በተቀናጀ የምርምር ፕሮጀክት (thematic research) “Description and Documentation of Languages and Cultures in Kafa Zone.” በሚል ርእስ የተጠና ነው። በዚህ ጥናት ውስጥ ያሉት መረጃዎች ከ2009 ታህሳስ እስከ 2012 ዓ.ም ጥር ድረስ የተሰባሰቡ ናቸው።

ይህ ጥናት ይዞት የተነሳው አላማ የፃራን ብሄረሰብ ትውፊታዊ እምነት መሠረታዊ ጽንሰ ሀሳብ ምንነት በእምነቱ መሪዎች እና በአማኙ የየእለት ህይወት ውስጥ የሚከወኑባቸውን መልኮች መተንተን ነው።

የጥናቱ ዘዴ የአይነት (qualitative) ወይም የትርጉም(interpretative) ባህርይ ያለው ነው። በመስክ ጥናት ላይ የተመሠረተ ቀዳማይ የመረጃ ምንጭ የጥናቱ ዋንኛ ግብአት ነው። ከመስክ መረጃ ለማሰባሰብ ምልከታ፣ ቃለ-መጠይቅና የቡድን ውይይት ዘዴዎች በአውዳዊ ሁኔታ በአገልግሎት ላይ ውለው መረጃው ከመስክ ተሰብስቧል። በመረጃ አቀባይነት የተሳተፉት የእምነቱ መሪዎች፣ አማኞች እንዲሁም ቀድሞ የእምነቱ ተከታይ የሆኑ ሰዎች ይገኙበታል። መረጃ የማሰባሰብ ስራው በጾታ ሴቶችንም ወንዶችንም፣ የእድሜ ስብጥሩ ወጣቶች፣ ጎልማሶችና አዛውንቶች ተካተውበታል። በተጨማሪም ከሚጠናው ርእሰ ጉዳይ አኳያ የእምነት መሪዎች፣ አገልጋዮች የተለያየ ክዋኔ መሪዎች እንዲሁም በተግባር የሚጠቀሱ ተመክሮ ያላቸው ግለሰቦች በጠቋሚ የመረጃ ሰጪዎች አመራረጥ ስልት ልምዳቸው እና ገጠመኛቸው በጥናት ውስጥ መካተቱ አስፈላጊ በመሆኑ ከሁለቱም ጾታ እንዲሁም በተለያየ እድሜ ደረጃ ያሉ መረጃ ሰጪዎች ተካተዋል።

## 2. የፃራ ብሄረሰብ ትውፊታዊ እምነት

የፃራ ህዝብ በአብዛኛው የትውፊታዊ እምነት ተከታይ ነው። በዚህ እምነት ውስጥ ያለን አንድ የብሄረሰቡ አባል እምነትህ ምንድን ነው? ተብሎ ሲጠየቅ ምላሹ "ኤቃ" የሚል ነው። የፃራ ብሄር ኤቃ ማለት ምንድን ነው? ከየት መጣ? ለሚለው ምላሽ የሚሆን መሰረታዊ የሚባል ትርክት አለው። በዚህ ትርክት ውስጥ የትውፊታዊ እምነቱን መሰረት፣ የእምነቱን መሪዎች የመሪነት ስልጣን ማን እንደሚሰጥ የእምነቱ ተከታዮች ለመሪዎቹ መገዛት እንዳለባቸው የሚተርክ ነው። የትረካው አጠቃላይ ጭብጥ የሚከተለው ነው።

የሪዶንቲ በሰማይ የሚኖር፣ ፀሀይ የሚያወጣ ዝናብ የሚያዘንብ ለሰው ልጅ የሚበላውንና የሚጠጣውን የፈጠረ፣ ለሙብረቅ ስልጣን የሰጠ፣ በአጠቃላይ ሁሉን የሰራ ሁሉን የሚያዝ ነው።

ኤቃ የየሪዶንቲ መልእክተኛ ሲሆን በተፈቀደለት መሠረት ይሰራል። የሪዶንቲ ኤቃን ከፈጠረ በኋላ በየሪዶንቲ ቦታ ሰይጣን መጥቶ ተቀመጠ። ኤቃ ሰይጣን የየሪዶንቲን ቦታ እንዲለቅ ደጋግሞ ቢጮህም ሰይጣን እሺ አላለውም። ሰይጣን ለኤቃ አልታዘዝ በማለቱ የሪዶንቲ ሰይጣንን ከቦታው እንዲያስነሳ ሙብረቅን አዘዘ። ሙብረቅ የየሪዶንቲን ትእዛዝ ተቀብሎ ብረሃኑን ሁለት ጊዜ ሰይጣን ላይ አበራበት። ሰይጣንም የሙብረቅን ብረሃን ፈርቶ የየሪዶንቲን ቦታ ለቀቀ። ሙብረቅም ሰይጣንን ወንዝ ውስጥ ጣለው፤ እስከ ዛሬ በወንዝ ይኖራል። ከዚያ በኋላ የሪዶንቲ ምድርን ለኤቃ ሰጥቶ "ሰው ላይ ሆነህ፣ ለሰው 'እንደዚህ አለ' ብለህ እየተናገርክ ሰው የሚሰጥህን ተቀብለህ በልተህ ኑር" አለው። ለሙብረቅ ደግሞ ሰዎች በትልቅነትህ ይመኑህ፤ መጀመሪያ የሚነቀለውን ጤፍ ይስጡህ። የተነቀለውን ጤፍ ሲሰጡህ በአይናቸው ሳያዩ ወደ ኋላ ዞረው ትልቅ ዛፍ ላይ ያስቀምጡልህ።

በዚህ መሠረት ሰው መብረቅን በትልቅነቱ አክብሮና ፈርቶ በየአመቱ ጤፍ ሲደርስ ምርቱን ከመሰብሰቡ አስቀድሞ የመጀመሪያውን ጤፍ ነቅሎ በትልቅ ዛፍ ላይ ያኖርለታል።

መብረቅ "ዳዳ" ይባላል። በፃራዎች ዘንድ መብረቅ ሰይጣንን በማባረሩ ዛሬም የጤፍ መስዋእት ይቀርብለታል። መብረቅ መስዋዕቱ ባይቀርብለት "ሰውን ሊገድል ይችላል" ተብሎ ይፈራል። ለመብረቅ መስዋእት የሚያቀርበው ሁሉም ሰው ወይም ሁሉም ጎሳ ሳይሆን የተመረጡ የፃራ ጎሳዎች ሌላውን ህዝብ በመወከል ነው። እነዚህ የፃራ ጎሳዎች አስር ሲሆኑ ለመስዋዕት የሚሆነው ጤፍ በማንኛውም ዛፍ ላይ ሳይሆን ዶብተና፣ ጎና እና ሲራ የሚባሉ ዛፎች ላይ ያቀርባል። ይህን የጤፍ መስዋእት ለመብረቅ የሚያቀርብ የተፈቀደለት ግለሰብ ሲሆን "መብረቅ ተከላካይ" በመባል ይጠራል። ይህ ሰው መስዋዕቱን ከማቅረቡ በፊት ለሀያ ቀናት ከሚስቱ ሳይገናኝ፣ ጎመንና ጎደሬ ሳይበላ ይቆያል። ለተጨማሪ ሶስት ቀናት ጫካ ውስጥ ያድራል። በአጠቃላይ ሀያ ሶስት ቀናትን በጥንቃቄ ካሳለፈ በኋላ በሌሊት ከአንድ እቅፍ የማይበልጥ ጤፍ ከነስሩ ነቅሎ ዛፍ ላይ ያስቀምጣል።

ለመብረቅ ከብትም ይታረዳል። ለመብረቅ የሚታረድ ከብት "ዳደሚያ" ይባላል። ከብቱ መልኩ ጥቁር ሲሆን ለመብረቅ ተብሎ የተሰጠ ከብት አንገቱ ገመድ አይነካውም፣ የትም ያድራል፤ የማንንም ሳር ይበላል፣ አውሬ አይበላውም። በመስከረም ወር ወንዶች[3] ከብቱን ይዘው ተራራ ላይ ሄደው አርደው ይበሉታል። ወደቤት ምንም አይነት ስጋ ይዘው አይመለሱም።

ኤቃ የሪዶንቲ ባዘዘውና በፈቀደለት መሠረት ይሰራል። የፃራም ህዝብ ኤቃ ከየሪዶንቲ የሚያገኝ መልእክተኛ እንደሆነ በማመን ከየእለት ተእለት እንቅስቃሴያቸው ጀምሮ በትልልቅ የህይወት ጉዳዮቻቸው ጭምር ትልቅ ስፍራ ይሰጡታል። በቀጣዩ ንኡስ ርእስ ኤቃን አስመልክቶ በዝርዝር ቀርቡዋል።

**2.1. ኤቃ**

ኤቃ ማለት መንፈስ ሲሆን መንፈሱ የሚያድረው ወንድ ላይ እንጂ ሴት ላይ አያድርም[4]። ኤቃ ያደረበት ግለሰብ ኤቀትሳ ይባላል። ኤቀትሳ ይሞታል እንጂ ኤቃ አይሞትም። አንድ ኤቀትሳ ሲሞት ኤቃ የሚተላለፈው ለአንድ ወንድ ልጁ ብቻ ነው። አንድ ሰው ብዙ ወንድ ልጆች ቢኖሩት ኤቃ በመረጠው አንዱ ልጅ ላይ ብቻ ያድራል። ወንድ ልጅ ከሌለው በመረጠው የወንድሙ ልጅ ወይም በቅርብ የስጋ ዘመዱ ወንድ ልጅ ላይ አልያም በአገልጋዩ (ቡርገ) ላይ ያድራል። ኤቃ ይከበራል። ይፈራል። ኤቃ ትንቢት ይናገራል፤ ሰዎች በሌሉበት የሚሰሩትን የሚያስቡትን ሳይነግሩት እንዲያውቅ የሪዶንቲ መርጦ ሾሞታል ተብሎ ይታመናል። ኤቀትሳ ማንኛውም ሰው ከሚያደርጋቸው ተግባራት ባለፈ በሰው አቅም እና ችሎታ የማይደረጉትን ያደርጋል። ለምሳሌ

---

[3] ሴቶች ግን "ዳደሚያ" ወደ ሚታረድበት አይሄዱም ስጋውንም አይበሉም።

[4]ድሮ "ዳትሰና" የምትባል ሴት ኤቃ ነበረች። ለኢቃ መሪው መስዋእት ሳታቀርብ ቀርታ በቅጣት ሞተች። ከዚያ በኋላ የሴት ኤቃ ቀረ።

ወንዞን እንደ የብስ ረግጦ ያልፋል። በሰው አቅም የማይደረግ ያደርጋል። ኤቀትሳ ሰው በሌለበት ያደረገውን፣ ወደፊት የሚገጥመውንም ጭምር በላዩ ያደረው መንፈስ (ኤቃ) እንዲያውቅ ያደርገዋል።

አንድ ኤቀትሳ ከሌላው ሰው የሚለየው ጸጉሩና ጺሙን አይላጭም፣ ተራው ሰው ከሚያደርገው ለየት ያለ ጨሌ ከተገኘ የነብር፣ ከጠፋ የአንበሳ ጥርስ አንገቱ ላይ ያደርጋል። በፃራ የወንድና የሴት መቀመጫ የተለያየ ስለሆነ ኤቀትሳ በወንዶች መቀመጫ ቦታ ይቀመጣል[5]። ከሰው ጋር ሲሄድ በስተቀኝ ራቅ ብሎ ይሄዳል። መንገድ ላይ ለሰላምታ ቆም ካለም በስተቀኝ ፈንጠር ብሎ እንጂ ተጠግቶ አይቆምም። ምክንያቱም በየመንገዱ ላይ የሚገጥመው ንጹህ ያልሆነ ሰው ሊሆን ይችላል በሚል ፍራቻ ነው። እንግዳ ሰው ካልሆነ ኤቀትሳን ማንም ሰው ለይቶ ያውቀዋል። ኤቀትሳ ቦርዴ ቤት ወይም መጠጥ ቤት አንዳንዴ ከማንኛውም ሰው ጋር ሳይሆን ከትልልቅ ሰዎች ጋር ይገባል። ኤቀትሳ ወደ መጠጥ ቤቱ ሲገባ ውስጥ ሰዎች ካሉ "አንድሮ"[6] በማለት በአክብሮት ስሙ ጠርተው እንዲገባ ይጋብዙታል። ባለመጠጥ ቤቷም ገለል ያለ መቀመጫ በአክብሮት ታሳየዋለች። መጠጡን የምታቀርበው በንጹህ እቃ እንጂ በማንኛውም እቃ አይጠጣም። ኤቀትሳ የከብት እና የዶሮ እንጂ የፍየል እና የበግ ስጋ አይበላም። ቀብር አይሄድም። ሬሳ ያለበት ቤት አይገባም። ሬሳ የወጣበት ቤት የሚገባው ከስድስተኛው ቀን በኋላ ነው። ሬሳ ያለበት ቤት ቢገባ ወይም ቀብር ቢሄድ፤ ልጆቹም እንዲሁ ቀብር ላይ ቢሄዱ ወይም ሬሳው ያለበት ቤት ቢገቡ ሊሞቱ ይችላሉ። ድንገት ሬሳ ያለበት ቤት ቢገቡ ወይም ድንገት ኤቀትሳ ያለበት ቤት ሰው ቢሞት ኤቃው ሮጦ መውጣት አለበት።

ፃራ ከስልሳ በላይ ጎሳ ያለው ሲሆን እያንዳንዱ የፃራ ጎሳ የራሱ ኤቀትሳ አለው። ጎሳ ሆኖ ኤቀትሳ የሌለው የለም። የየጎሳው ኤቃ ግለሰቡ ቢለዋወጥም (ቢሞትም) የማይለወጠው ኤቃውና መጠሪያ ስሙ ነው። ለምሳሌ የጎሳውን ስም እያስቀደምን የኤቃውን ስም በማስከተል ጥቂት ምሳሌ እንመልከት። "ዟ"- ቡሺ፣ ዱገትሳ- መጺ፣ ጪሸትሳ-ቦረንዲ ጉብቶሲ-ዛጊዳ፣ አልማኒ-ቦቃትሳ፣ ጎብቶስ-ሹሙትሳ፣ ባንካን-ጋይዘትሳ፣ አማ-ገረመንዞ፣ ባንካን-አዲቦ፣ ቢርተትሳ-ዳሪ ይገኙበታል።

በስልጣን እኩል ደረጃ ካላቸው ኤቃዎች መካከል ለምሳሌ፤ አዲቦ፣ ቡሼ፣ መጺ፣ ኡንዲ፣ አልሚኒ፣ ጉብቶሲ፣ ባንካኒ ይገኙበታል። እነዚህ ኤቀትሳዎች በተለያዩ ቀበሌዎች የሚኖሩ ሲሆን በአንድ ቀበሌ ሁለት ኤቀትሳዎች ሊኖሩ ይችላሉ። ለዚህ ጥናት መረጃ የሰጡን ኤቀትስ ቦንገትስገዝ[7]

---

[5]በማንኛውም ሰው መኖሪያ ቤት ከምሰሶ በላይ በስተግራ የወንድ መቀመጫና መኝታ ሲሆን ከምሰሶ በታች በስተቀኝ የሴት መቀመጫ እና መኝታ ነው።

[6] የኤቀትሳ የአክብሮት ስም ሲሆን ይህ የአክብሮት ስም ኤቃ ላልሆነ ሌላ ሰው አይጠቀሙም)

[7] ለዚህ ጥናት መረጃ ለማሰባሰብ የተመረጠው አካባቢ ያሉት ኤቃ ቦንገትገዝ ሲሆኑ መጠሪያ ስማቸው አቶ ታመነ ተሰማ ይባላል። ቦንገትስ ገዝ-የአቶ ታመነ መጠሪያ ማለት ሲሆን ገዝ ማለት መንፈሱን የሚሸከመው አሸከር ማለት ነው። ቡርገር ደግሞ መንፈሱን የተሸከመውን የሚያገለግል ማለት ነው። አቶ ታመነ እድሜያቸውን ስንት እንደሆነ አያውቁትም። በግምት ከስልሳ አመት በላይ ይሆናቸዋል። አስር ልጆች ነበሯቸው፤ ስድስቱ ሞተዋል። ሶስት ሚስት አግብተዋል። የመጀመሪያ ሚስታቸው ሞታለች። ሶስተኛ ሚስታቸው በቅርቡ ጥላቸው ወደ ቤተሰቧ ተመልሳለች። ሚስታቸው የሄደችበትን ምክንያት ሲገልጹ ከፈረስ ወድቄ ማረስ ስለማልችል፤ "ማን ያበላኛል ብላ ጥላኝ ሄደች" ብለዋል። እሳቸው ይህንን ይበሉ እንጂ በአካባቢው ያሉ መረጃ ሰጪዎች ምክንያቱ ባህሉን ባለማክበራቸው ነው ይላሉ። አቶ ታመነ እንደ ኤቃ አብዛኛው ሰው አክብሮት አይሰጣቸውም። ምክንያቱ ደግሞ ሁለት ሚስቶቻቸው

ናቸው። ቦንጎትስገዝ የኅሳም የኤቀትሳም መሪ ሲሆኑ በስራቸው ያሉ ኤቀትሳዎች ዝርዝር፤ ትኋኔ፣ ሀርሺ፣ በሪ፣ አከማሪ፣ ዲንገሬ፣ ቦንገሬ ሃዳና ቦንጎቾ የሚባሉት ይገኙበታል።

እነዚህ ከላይ የዘረዘርናቸው እያንዳንዱ ኤቃ አኩል ነው። ሆኖም በፃራ ብሄር ዘንድ ጎልቶ የሚሰማው ቡሺና አዲቦ ናቸው። አንድ ሰው እንቅፋት ሲመታውም አዲቦ ወይም ቡሺ ይላል። ምክንያቱ ይሄ ነው ለማለት ቢያስቸግርም ሁለቱ ግን ገነው የሚታወቁ ናቸው። አንዱ ከሌላው ጎልቶ ስሙ የሚነሳበትን ምክንያት ሲጠቅሱ የየግለሰቦች አንዱን ከፍ አድርጎ ማየት ወይም ማበላለጥ በግለሰቦች ዘንድ የሚመጣው ኤቀትሳው እንዲፈታ የተሰጠውን ውስብስብ ችግር የፈታበት መንገድ፣ የስእለት ፈጥኖ መድረስ፣ በጥቅሉ በማህበረሰቡ ዘንድ አውቆም ይሁን በአጋጣሚ ለችግሮች መፍትሄ ሰጪ፣ ቁጡ ስእለት ሰሚ ተብሎ ቦታ ይሰጠዋል።

አንድ ሰው ኤቀትሳ መሆኑን ወይም ለኤቃነት መመረጡን የሚያውቀው ቀዳሚው ኤቀትሳ ከሞተ በኋላ ነው። አንድ ኤቀትሳ ቢያረጅም በህይወት እያለ መንፈሱ ወደ ሌላ ሰው አይተላለፍም። ግለሰቡ ከሞተ በኋላ በቤተሰቡ ወንድ ልጅ ላይ፣ የወንድሙ ልጅ የአጎቱ ልጅ ላይ ሊያርፍ ይችላል። የፈለገውን የሚመርጠው ኤቃው እራሱ ነው። አንዳንዴ ግን የቡርገዋ ልጅ ላይ ወይም የአፈቾ ልጅ ላይ ሊያርፍ ይችላል። አንድ ኤቀትሳ ኤቃው እንደመረጠው በተለያየ መንገድ ያውቃል። ለምሳሌ አቶ ታመነ የአባታቸው ኤቃ እሳቸውን መምረጡንና እንዴት ኤቀትሳ እንደሆኑ ሲገልጹ፡-

> አባቴ አቶ ተሰማ ኤቀትሳ ነበር። አባቴ ከሞተ በኋላ መንፈሱ መርጦ ያዘኝ። ኤቀትሳ መሆኔ የታወቀው ያደረብኝ የአባቴ ኤቃ ያስጮኸኝ ስለነበረ ነው። በኋላ ከቤቴ አስወጥቶ ሙንጢ የሚባል ፍል ውሃ ያለበት ጫካ ውስጥ ወሰደኝ። ውሃው አፈር የተቀላቀለ ደም የሚመስል ሲሆን እየጮህኩ ጫካውን እየዞርኩ ያንን ውሃ እየጠጣሁ በዚያው ውዬ አድር ነበር። ሌላ ኤቃ እዚያ መጥቶ እኔ ላይ ያደረውን ኤቃ ለምኖ፣ አዲስ ልብስ አልብሶ ለአንድ አመት ጫካ ውስጥ ውሃውን ሳልነካ ሴት ሳላይ፣ ሴቶችም ሳያዩኝ ደጅ በመጥናት እንድቆይ አደረገኝ። በኤቃው ጥቁር በሬ እዚህ እኔ የምኖርበት ቀበሌ ላለው ኤቀትሳ እንድሰጥ ታዘዝኩ። የታዘዝኩትን አድርሼ በኤቀትሳው ተመረቅኩ። የመረቀኝ ገረመንዞ የሚባለው (ወይም እኔ ላይ ያደረ ኤቃ አቻው የሆነ) ነው። በእኔ ስር ያሉት መጡ እና ደስታ ሆነ። ይህን ሁሉ ያዘዘኝ ኤቃው ነው። አሁን የምሰራው ሁሉ እንዲሆንልኝ መርቆኛል።[8]

አቶ ታመነ ኤቀትሳ መሆናቸው ሲረጋገጥ በወቅቱ በቦታው የነበሩት በእድሜ አቻ የሚሆኑት የእምነቱ ተከታይ ሲገልጹ፤ "ከጫካ ሲወጡ አቶ ታመነን ሊቀበሏቸው የተሰበሰቡት ኤቀትሳዎች

---

እህትማማቾች ስለሆኑ ህዝቡ "ኤቃ ሆነው ባህሉ የማይፈቅደውን እህት አማቾች እንዴት ያገባሉ!" በሚል ነው። ሆኖም ለማንኛውም ኤቃ በአመት የሚሰጠውን ግብርና ስእለት አያስታጉሉም።

[8] ቃለመጠይቅ፣ አቶ ታመነ ተሰማ (ኤቀትሳ)፣ 15/4/2010ዓ.ም።

በሙሉ እቤት እስከሚገቡ ድረስ በጣም ይጮሁ ነበር።[9]" መራቂው ኤቀትሳ አቶ ታመነ ከሰዎች እንዲሁም ከሚስቱ ጋር ያለው ግንኙነት እንዴት መሆን እንዳለበት በመንገር ከዚያ ቀን ጀምሮ የኤቀትሳን ተግባር መፈጸም ጀመሩ። አቶ ታመነ ከሰላሳ አምስት አመት በላይ ኤቀትሳ ሆነው እያገለገሉ ይገኛሉ።

አንድ ኤቀትሳ ከመኖሪያ ቤት ራቅ ባለ ስፍራ መንፈሱ ባዘዘው ወይም በመረጠው ቦታ ላይ ቋሚ የአምልኮ ስፍራ ይኖረዋል። ይህ የአምልኮ ስፍራ ኤቀ ኬታ በመባል ይታወቃል።

**2.2 ኤቀኬታ**

ኤቀ መንፈስ ሲሆን ኬታ ቤት የሚል ትርጉም አለው። "ኤቀኬታ" አንድ ኤቀትሰ ከኤቃው የሚገናኝበትና ቋሚ የአምልኮ ስፍራ ነው። ኤቀ ኬታ ዛፎች ባሉበት አካባቢ ከመኖሪያ ቤቶች ራቅ ብሎ ኤቃ በፈቀደበት ቦታ ይሰራል። አንድ ኤቀትሳ አንድ የአምልኮ ስፍራ አለው።

ኤቀኬታ ራሱን የቻለ ቤትና አጥር ያለው የአምልኮ ስፍራ ነው። በስፍራው በመገኘት በምልከታ ያስተዋልነው ኤቀ ኬታ የግርግዳ ምርጊት የሌለው፣ በጭራሮ የተሰራ፣ ጣራው በሰንበሌጥ የተሸፈነ፣ መካከል ላይ ምሰሶ ያለው ከአራት ሰው በላይ የማያስገባ ነው። ኤቀኬታ ውስጥ ከቡርዥ(አገልጋይ) እና ከኤቃው ውጭ ማንም አይገባም። የኤቃው አጥር "ኤማ" በሚባለው ዛፍ ይታጠራል። ኤማ የሚባለው የዛፍ ዘር ለአጥር መዋል ብቻ ሳይሆን ችግኙ በአጥሩ ዙሪያ ይተከላል። ኤማ ከሌላው እንጨት ተለይቶ ለኤቀኬታ የተመረጠው ምስጥ ስለማይበላው ነው። አንዳንዴም ስእለት ተስለው የኤማን እንጨት ለኤቃ ያመጣሉ። በኤቃ የአምልኮ ስፍራ የበቀለ ዛፍ አይቆረጥም ቢወድቅ ወይም መቆረጡ የግድ ሲሆን በዚያው ስፍራ በማገዶነት ያገለግላል። ዛፍ የማይቆረጥበት ምክንያት የመንፈሱ ማረፊያ ነው ተብሎ ስለሚታመን ቢቆረጥ መንፈሱ ከአካባቢው ርቆ ሊሄድ ይችላል በሚል ፍራቻ ነው።

ኤቀትሳ ከመንፈሱ የሚገናኝበት ጎጆ የሚገኘው ሁለት አጥር ታልፎ ሶስተኛው ክፍል ሲሆን ይህ ክፍል ኬሸኬላ ይባላል። ኤቀትሳው የሚቀመጥበት በአልጋ መልክ ከእንጨት የተሰራ ርብራብ ያለው ሲሆን "ቆላ" ይባላል። ቆላ በኤቄ ኬታ መካከል ባለው ኤቀትሳው በሚቀመጥበት ክፍል የሚቀመጥ ሲሆን ቆላ ይባላል። ቆላ ቃጭል የሚመስል ከብረት የተሰራ ሲያንቀሳቅሱት እንደ ቃጭል ድምጽ የሚሰጥ ብረት ነው። ኤቀትሳው ላይ ያደረው ኤቃ ሲናገር ኤቀትሳው ቃጭሉን እየመታ ያስጮሀዋል። ጎንፓ-የቃጭሉ መስቀያ እንጨት ምሰሶው ላይ ይሰቀላል። ማንኛውም እሱን የመሰለ እንጨት ጎንፓ አይባልም።

ኤቀኬታ ምሰሶ ያለው ሲሆን ከጣራው በላይ አልፎ ወጥቶ ይታያል። መንፈሱ ያዘዘውን ዘንባባ ወይም ሌላ ቅጠል ይደረግበታል። በምሰሶው ስር ኤቀትሳው ቡና የሚጠጣበት ስኒ እንዲሁም ከመንፈሱ ሲገናኝ የሚይዘው "ቤና" (ጨሌ) በቋሚነት የሚቀመጡ ሲሆን ሌላ እቃ የለበትም። ኤቃ ከመንፈሱ ለመገናኘት ሲፈልግ ቤናውን በእጁ ይይዛል። ቤናው ኤቄኬታ ውስጥ ምሰሶ ላይ

[9] ቃለመጠይቅ፣ አቶ ኢርታንቆ ለገሰ፣ 30/8/2010 ዓ.ም።

ተሰቅሎ ይቀመጣል። ማንም ሰው ወደዚያ የአምልኮ ስፍራ ገብቶ ይህን ቤና አይነካም። ምክንያቱም ቤናውን የነካ መንፈሱን እንደነካ ተቆጥሮ ቅጣት ይደርስበታል ተብሎ ይታመናል። በኤቀኬታ ውስጥ ያለ ምክንያት የሚገባ ሰው የለም "እባብ አለ" ስለሚባል ይፈራል። ከእንሰሳት የማይገቡ በግ እና ፍየል ናቸው። ኤቀ ኬታ ማንኛውም ሰው እንዳይገባ የሚከለክለው ለእምነቱ ያለው አክብሮት እንጂ የአጥሩ መዝጊያ በር ጥብቅ ሆኖ አይደለም።[10]

ከመጀመሪያው አጥር አልፎ ወደ ሁለተኛው ኤቀ ኬታ ግቢ ማለፍ የማይችሉት ሽከላ ሰሪና ቀጥቃጭ የሚሏቸው የማህበረሰቡ አባላት እና ለጊዜው "መጥፎ እግር[11]" የሚባሉት ናቸው። ኤቀትሳው ከኤቃው የሚገናኝበት ክፍል የሚገቡት ኤቀትሳው እንዲሁም ቡርገ እና ጦፎቻ ናቸው። ለኤቀትሳ ምግብ የምታበስለዋ ጣፎቻ ስትሆን የሚቀምሰው ደግሞ ቡርገ ነው። ቡርገ እያለ ጦፎቻ ለኤቀትሳ ቀምሳ አትሰጥም ቡርገ ከሌለ ግን ቀምሳ ትሰጣለች።።

ኤቃ በቋሚነት በሳምንት መንፈሱ ባዘዘው ዕለት የአምልኮ ስፍራው ይውላል። የአምልኮ ስፍራ መቼ እንደሚሄዱና ሄደው ምን እንደሚያደርጉ አቶ ታመነ ሲገልጹ፣

> እሁድ ኤቀኬታ እውላለሁ። አልበላም። አልጠጣም። እጄን አልታጠብም። መጀመሪያ ወደ ኤቃ ኬታ የምገባው እኔነኝ። እኔ የማውቀው እስከምገባ ብቻ ነው። ከገባሁ በኋላ ራሴን አላውቅም። እኔ መጀመሪያ ከተናገርኩ በኋላ (ከመንፈሱ ከተገናኘሁ በኋላ) ስድስቱ ቡርገር ጮህው እኔ ወዳለሁበት ይገባሉ። የተናገርኩትን የሚነግሩኝ ለሌላው የሚያሰሙ ቡርገሮቼ ናቸው። ይህን ካደረኩ በኋላ እኔም ሆንኩ በእኔ ስር ያሉት ቡርገሮች ነጻነት እናገኛለን። ከኤቀ ኬታ ውጭ ሆኜ መንፈሱ እንድናገር ካደረገኝ እታመማለሁ። መታመሜን ግን አላውቅም። ሰዎች ኤቄኬታ ያደርሱኛል፤ ለቀናት በዚያ ቆይቼ ጤናዬ ይስተካከላል።

ኤቀ ኬታ ሳይሄድ በመኖሪያ ቤቱም እያለ ባለጉዳይ መጥቶ መንፈሱ በኤቀትሳው ላይ ሆኖ እንዲናገር ሲፈለግ መንፈሱ ይመጣል። ኤቀትሳ በመንፈስ የሚናገረው በብዛት ሌሊት ነው። አንድ ባለጉዳይ ኤቀትሳ ዘንድ ሲሄድ እና መንፈሱ እንዲናገር ሲፈለግ ባለጉዳይ ብቻውን ሳይሆን ሌላ ጉዳዩን የሚያስረዳ ሰው ይዞ ይሄዳል። ቡርገ ኤቀትሳው ባለበት ቅርብ ቦታ ስለሚሆን መንፈሱ እንዲመጣ ሲፈለግ ቡርገም ወደ ኤቀትሳው ይመጣል። ኤቀትሳው የሚናገረውን የሚሰማው ቡርገ ነው። መንፈሱ ሲመጣ ባለጉዳዩም ባለጉዳዩን አቅራቢውም እንዲቆሙ መንፈሱ በቡርገ በኩል ያዛል። ባለጉዳዩን በስተቀኝ ወይም በስተግራ ቁም ብሎ የሚያዘው መንፈሱ ነው። ኤቀትሳው መንፈሱ ሲያናግረው በአንድ እጁ ደረቱን ይመታል። በአንድ እጁ ቃጭሉን ያስጮህል።

[10]ቃለመጠይቅ፣ አቶ ደንበላሽ ሺንደመር (ቡርገ) 20/4/2009 ዓ.ም።

[11]መጥፎ እግር ማለት ለምሳሌ የወር አበባ ላይ ያለች ሴት፤ አይነ ምድር የረገጠ ይገኙበታል።

ኤቀትሳው ከመንፈሱ ተገናኝቶ ከጨረሰና ወደ ራሱ ከተመለሰ በኋላ ይመርቃል። አቶ ታመነ በምርቃታቸው የሚገኘውን ትሩፋት ሲገልጹ "ረሀብ ያልኖረው፣ እኛ እዚህ አጠገባችን ካለው ከተራራው መንፈስ ጋር ስለተስማማን፣ መንፈሱን ስላከበርን ሌላውም ሰው እኛን ካከበረ ሰላም ይሆናል።"

ኤቀትሳው ኤቀኬታ በሚውልበት እለት ሚስቱ ንጹህ ከሆነች (የወር አበባ ላይ ካልሆነች) ቡና ታፈላለች። ኤቀትሳ በአምልኮ ስፍራው ሲውል ጉዳይ ያላቸው ሰዎች ይሄዳሉ። ኤቀኬታ የሚመጡ ሰዎች የተለያየ ምክንያት ያላቸው ሲሆን ለምሳሌ ሰው የታመመበት የህመሙን ምክንያት ሊጠይቅ። የተቸገረ ችግሩ እንዲፈታ ስእለት ለመሳል፤ ስእለቱ የተሳካለት፣ ስእለቱን ለመስጠት ይሄዳል። ማንኛውም ሰው ጉዳዩን ለኤቃው ለመንገር ወደ ኤቄ ኬታ ወይም ወደ መኖሪያ ቤቱ በመሄድ እንጂ አጋጣሚ መንገድ ላይ ሲገናኙ አይነገርም።

ኤቀትሳው ለተጠየቀው ከመንፈሱ ምላሽ ለማግኘት በመንፈስ ከመናገሩ ውጭ ኤቄ ኬታ ቡና ተፈልቶ ቡና የጠጣበትን ሲኒ እያየም ይናገራል። ስኒ ከማየቱ በፊት "የሪዶንቲ" እውነቱን ገልጠህ አሳየኝ ብሎ ይለምናል። ለምሳሌ ስለታመመ ሰው ተጠይቆ መንፈሱ ያሳየው ታማሚው እንደሚሞት ከሆነ የሚሰጡትን ገንዘብ አይቀበልም፤ ይሞታል ብሎም አይነግራቸውም። ታማሚው እንደሚድን ከተገለጸለት የህመሙን ምክንያት እና ከህመሙ ለመፈወስ ማድረግ ያለበትን ይናገራል። ጠያቂዎቹ ከአስር ብር የማይበልጥ ገንዘብ ይሰጡታል።

**2.3 ኬያ (ስእለት)**

ኬያ ማለት ስእለት ማለት ነው። የኤቃ ትውፊታዊ እምነት ተከታዮች የሚፈልጉት፣ የተመኙት እንዲሆንላቸው ችግራቸው መፍትሄ እንዲያገኝ ለኤቃ አንዳንዴ ለሙብረቅ የተለያየ አይነት ስጦታ ለመስጠት ሌላ ሰው እየሰማም ይሁን በሌለበት (ለራሳቸው) ቃል ይገባሉ። ለኤቃ ስእለት ተስለው ስእለቱ ተሳክቶ ሲሳሉ የነበረው ኤቀትሳ ቢሞት የእሱ ኤቃ ላረፈበት ኤቀትሳ ስእለቱን ይሰጣሉ። ምክንያቱም ግለሰብ ሞተ እንጂ ኤቃ አልሞተም። በትውፊታዊ እምነት ተከታዮች ዘንድ ለኤቃ ስእለት መሳል የተለመደና የእምነቱ አንድ አካል ተደርጎ የሚወሰድ ነው።

የስእለት ምክንያት የተለያየ እንደሆነው ሁሉ የስእለቱም አይነት የተለያየ ሊሆን ይችላል። ለምሳሌ ገንዘብ፣ ከብት፣ እህል፣ ልጅ፣ እንጨት፣ የሚበላ ወይም የሚጠጣ ነገር ሊሆን ይችላል። የስዕለት አይነቶቹ የተለመዱና የሚታወቁ ሲሆን ለስእለት የሚሆኑና የማይሆኑትም ይታወቃሉ። ለምሳሌ ፍየልና ቡና ለኤቃ ስለማይሰጥ ስእለት ውስጥ አይገባም። በአብዛኛው ለኤቃ ከሚሳሉት ዶሮ፣ ቦርዴ፣ በሬና ገንዘብ ይገኙበታል። ቀደም ሲል ልጃገረድ በጣም ስትታመም በተለይ ገረመንጀ ለተባለው ኤቀትሳ "ገረመንጀ እባክህ አትግደላት አድናትና የአንተ አሽከር ያግባት[12]" ብለው ይሳሉ ነበር። ልጅቱ ከዳነች በቃላቸው መሰረት ይሰጧታል።ገረመንጀ የተባለው ኤቀትሳ በስእለት የተሰጠችው ልጅ ስታድግ ሊያገባት ይችላል ወይም ለአገልጋዮቹ በኤቀትሳው ፈቃድ ትዳራለች።

[12] ቃለመጠይቅ፣ አቶ ሺንደሚሬ አሸቱ፣ 2/4/2010ዓ.ም።

የስእለት ምክንያት እንሰሳት በተከታታይ የሚሞቱበት ግለሰብ ከብቶቹ እንዲረቡ ለምሳሌ “እኔ ቤት ውስጥ ከብቶች ከረቡ ከከብቱ መካከል አንድ ወይፈን አመጣለሁ”[13] ይሳላል። ለስእለት የሚሆን ከብት ወይፈን ወይም በሬ እንጂ ጊደር ወይም ላም አትሆንም። ምክንያቱም ሴት እንስሳ ለመስዋእትና ለስእለት አይሆንም[14]። በቃሉ መሠረት ከተሳካለት ይሰጣል። በኤቃ ትውፊታዊ እምነት ተከታዮች ዘንድ ልጅ ለመውለድ መሳልም የተለመደ ነው። ለምሳሌ ወንዶች ልጆችን ደጋግማ የወለደች እናት ለምን እና እንዴት እንደተሳለች እንደሚከተለው ገልጻለች።

> ሶስት ወንድ ልጆች አከታትዬ ወልጄ አራተኛ እንደ ጸነስኩ ኤቀትሳ ዘንድ ሄጄ ሴት እንድትሆንልኝ ተሳልኩ። ስዕለቴን ከሰማኝ አስር ብር በእጄ ሳልነካ በጥርሴ ብቻ ነክሼ አመጣለሁ የሚል ነበር። የተሳልኩት ሲሳካልኝ በስእለቴ መሰረት እኔ ልጄን አቅፌ፣ በጥርሴ አስር ብሩን ነክሼ፣ ባሌ ቦርዴ ይዞ ሄድን። ኤቀጎራ የመጀመሪያው አጥር ዘንድ ስደርስ በንብርክኬ በመግባት የነከስኩትን ብር እዚያ ጣልኩ። ልጅቷ በእግሯ መሄድ ከቻለች ወዲህ ጤፍ ሲደርስ በየአመቱ አስር ብር በጥርሴ ይዤ፣ ባሌ ቦርዴ ይዞ እንሄዳለን። ይህን በየአመቱ አዲስጤፍ ሲደርስ ካላደረኩ ልጄ ችግር ይደርስባታል ወይም ትሞታለች ብዬ እፈራለሁ።[15]

ለኤቃ ስእለት ተስሎ በቸልተኝነት ወይም በመርሳት ያላደረሰ ግለሰብ በቤተሰቡ ወይም በራሱ ላይ አንዳች ሳንካ ይደርስበታል ተብሎ ይፈራል። ስእለት ተስሎ የረሳ ግለሰብ ከሆነ የሳንካውን ምክንያት ኤቀትሳው ዘንድ ሄዶ ሲጠይቅ “እንዲህ አይነት ስእለት ተስለህ ሳታደርስ ቀርተህ ነው” ብሎ ይነግረዋል። በቸልተኝነት ስእለቱን ያላደረሰ ግለሰብ ደግሞ በቤተሰቡም ሆነ በራሱ ላይ የትኛውም አይነት ችግር ቢደርስ ስእለት ተስዬ ባለማድረሴ ነው ብሎ ያምናል።

ኤቀትሳ በስእለት የሚመጣለትን ገንዘብም ሆነ ከብቶች በሙሉ ለግል ጉዳዩ ብቻ ማዋል አይችልም። ለምሳሌ ሚስት ሊያገባ ቢፈልግ የስእለቱን ከብት ለጥሎሽ አይሰጥም። ለኤቀትሳ በስእለት የገባ ከብት “ኤቀ ሚያ”[16] ይባላል። ሰው በሚሰበሰብበት እለት መንፈሱ ባለበት (ኤቄ ጎራ) ታርዶ ይበላል። ለስእለት የመጣ ከብትም ሆነ ሌላ በመኖሪያ ቤት ውስጥ አይታረድም አይበላም። ምክንያቱም መንፈሱ “እኔ እየተራብኩ እናንተ ትበላላችሁ” ብሎ የሚበሉትን ሰዎች በተለያየ መልክ ሊቆጣና ሊቀጣ ይችላል፣ ተብሎ ይታመናል። ስለዚህ ለኤቃ የተሰጠ የሚበላ ወይም የሚጠጣ ስእለት የእምነቱ ተከታዮች ባሉበት በኤቀኬታ ይበላል፤ ይጠጣል።

ስእለት የሚሳሉት ለኤቃ ብቻ ሳይሆን ለመብረቅም ነው። ለመብረቅ የሚሳሉት ከብት ነው። ከብቱ (ዳደሚያ) ስእለቱ የተለያየ ምክንያት ሊኖረው ይችላል። ለምሳሌ ገንዘብ አልበረከት

[13] ቃለመጠይቅ፣ አቶ ሺንደሚሪ እሸቱ፣ 2/4/2010ዓ.ም።

[14] ጊደር ለግብር ከተሰጠ እህል ይጠፋል፣ የተዘራው አይበቅልም። እንዲሁም ስእለት ላመጣ የሚመረቀው ምርቃት “ወንድ ልጅ ውለድ፤ አንተ ቤት ባለው በሬ እረስ” ተብሎ ነው።

[15] ቃለመጠይቅ፣ ወ/ሮ ሙላ ሙልጌቲ፣ 6/4/2010ዓ.ም።

[16] ለጥሎሽ የሚሰጥ ከብት ደግሞ “አሽሚ” ይባላል።

ያለው፣ ከብት አልረባ ያለው፣ ሌላም ሌላም የተቸገረ ችግሩን ገልጾ "የአባቴ መብረቅ ሆይ ይህን ካደረክልኝ በሬ እሰጣለሁ፣ ወይፈን እሰጣለሁ ብሎ ይሳላል። ስእለቱ ሲሳካ ለመብረቅ መስዋእት የሚሆነውን ከብት መልክ መርጦ ከቤቱ አውጥቶ ለሰው ለቤተሰቡ ተናግሮ ይሰጣል። ሰውም ያውቃል አይነካውም። ያ ከብት አይሸጥም አይታረድም። የሚታረደው በመስከረም ወር፣ የሚታረድበት ቦታ የተሳለው ሰው አቅራቢያ የሚገኝ ደን ያለበት ተራራ ላይ ነው። ከብቱን የሰጠው ሰው አብሮ ይሄዳል። ስጋው ወደ ቤት አይመጣም ሴቶች አይበሉትም።

> "ዳደሚያ" ሲታረድ ቆዳው ጭንቅላቱ የፊት እግሮቹ ጥፍር፣ ጭራው በጥንቃቄ ሳይነኩ ከቆዳው ጋር እንደተያያዙ ይቀራሉ። ሌላው ስጋ ከተበላ በኋላ ቆዳው ተመልሶ በህይወት ያለ በሬ አስመስለው ባረዱበት ተራራማ ቦታ (ጫካ ያለበት) አቁመውት ይሄዳሉ። ድንገት ያን የቆመ ቆዳ ያየ ሰው በህይወት ያለ በሬ ይመስለዋል።[17]

በፃራ ብሄረሰብ ሰው ሲታመም፣ ከብት አልረባ ሲል ተመሳሳይ ጾታ ያላቸው ልጆች ደጋግመው ሲወለዱ፣ ልጆች በተደጋጋሚ ሲሞቱ እና በሌሎችም ምክንያቶች ለሚፈጠሩ ክስተቶች ከኤቃ፣ ከመብረቅ መንፈስ ወይም ቀድመው ከሞቱ ዘመዶቻቸው መንፈስ መቆጣት ጋር እንደሚያያዝ ያምናሉ። ይህ ችግር ደግሞ በስእለት ይፈታል ብለው ስለሚያምኑ ስእለት መሳል የተለመደ የየእለት ክዋኔ ነው። ስእለት ተስሎ ሲደርስ በወቅቱ አለመክፈልም ሌላ ተጨማሪ ችግር ሊያመጣ ይችላል ተብሎ ስለሚፈራ ስእለትን በጊዜው መክፈል የግድ ነው።

የኤቃ ትውፊታዊ እምነት ተከታዮች ለኤቀትሳ የተሳካላቸው ስእለት የሚከፍሉት በአብዛኛው ኤቀትሳ ወደ አባቱ በመንፈስ ሲሄድ ወይም ሲመለስ ነው። አንድ ኤቀትሳ ወደአባቱ ሄደ የሚባለው የካቲት መጀመሪያ ከጥር 21 በኋላ ነው። ኤቃ ሊሄድ ሲል በኤቀ ኬታ የስእለት ከብት ወይም እሱ ያዘጋጀው አልያም አማኞቹ ያመጡት ካለ ብዙ ሰው ተሰብስቦ ታርዶ አማኞቹ አገልጋዮቹ ባሉበት ይበላል። የሚታረድ ባይኖርም ሌላ ምግብ ተበልቶ ቦርዴ ተጠጥቶ ኤቀትሳው ይመርቃል። ምግብ የተሰራበት የተበላበት የተጠጣበት እቃ ታጥቦ ቤቱ ተጠርጎ፣ የኤቀኬታ በር ተዘግቶ ይወጣሉ። ኤቀትሳውም ሆነ ሌላው ሰው ወደየቤቱ ይሄዳል። ከዚህ ቀን ጀምሮ ኤቀትሳው ሄዷል ("ቶሬመንቤ")[18] ወይም አባቱ ዘንድ ሄዷል ("ኤቃባይ ነዳን") ይባላል። ኤቃ ወደ አባቱ ሄዶ እስከሚመለስ "ኤቃ እንዴት ባዶ ቤት ይመጣል" ይባላል። ኤቀ ኬታውን የትውፊታዊ እምነቱ ተከታዮች መንጥረው ጸድቶ ቦርዴ እና ምግብ ይዘጋጃል። ስእለት የሚከፍል ካለ ያመጣል። ቦርዴ እንዲሁም የተገኘው ምግብ እንደየ ሰው አቅም ሁሉ ነገር ይዘጋጃል። ኤቃ ከአባቱ ዘንድ ተመልሶ መጣ ("ካሞሽቴን") ይባላል።

ኤቃው ተመለሰ የሚባልበት ወቅት ሀይለኛ ንፋስ ያለበት ግንቦት አካባቢ ስለሆነ "ንፋሱ ሊመልሰው ነው" ይባላል። በኤቀ ኬታ ምግቡ መጠጡ ተዘጋጅቶ ቡና ተፈልቶ ኤቃው ተመለሰ

---

[17] የቡድን ውይይት፣ አቶ አይከሮ ጊንዳቤ፣ አቶ አካሉ እልኩ፣ አቶ አቱሞ ዶርጫዬ፣ አቶ ታደሰ ጊንዳቤ እና አቶ ኬሮ አይሻሌ 1/4/2012 ዓ.ም

[18] በጻራ ቋንቋ ለማንኛውም ሰው ለምሳሌ ወደታች ሄደ ለማለት "ኤቃቶረ ሀሞስ" ይባላል። የኤቃው ግን ሄደ የሚለው ቃል ይለያል።

ይባላል። ኤቀትሳው ከመኖሪያ ቤቱ ወደ ኤቃኬታ ይሄዳል። ኤቀትሳ የሆነው ግለሰብ ግን በአካል አይሄድም። አይመጣም። የሚሄደውም የሚመጣውም መንፈሱ ወይም ኤቃ ነው። ስለዚህ መሄዱም ሆነ መመለሱ በመንፈስ እንጂ በአካል አይደለም። ተመለሰ የሚባለው የሚበላ የሚጠጣው በኤቃኬታ ተዘጋጅቶ ከመኖሪያ ቤቱ ወደ ኤቀኬታው በመሄዱ ነው። የትውፊታዊ እምነቱ ተከታዮች ተሰባስበው የተዘጋጀው ምግብና መጠጥ ተበልቶ ተጠጥቶ ወደ እርሻ ስራ ወደ ምንጣሮ ለመሄድ ኤቀትሳው ይመርቃል። የሚቀጥለው ወር "ኢሰ ዶዛ" ወይም አንድ ብሎ ይጀምራል።

የእርሻ ስራ እና ትውፊታዊ እምነት የተያያዙ ናቸው። የፃ/ራ ህዝብ የተለያዩ አዝእርቶችን ይዘራሉ። "ከአያቶቻችን ጀምሮ ለእኛ የተሰጠ ነው" ብለው የሚያምኑትን አምርተው ወይም በእሸትነቱ ከመመገባቸው በፊት ለኤቃ እንዲሁም ቆሉ ለተባለው በጫካ ለሚኖር መንፈስ እና ለቀደሙ አያቶቻቸው የሙት መንፈስ ይሰጣሉ። አዝመራው ደርሶ ለምግብነትም ሆነ ለገበያ ከመዋሉ በፊት በየቤቱ የአዲስ እህል መቅመሻ በጤፍ ብቻ በሚዘጋጅ ምግብና መጠጥ ተዘጋጅቶ በየቤቱ ድግስ ይደገሳል። ይህም ገኔ ጌዛ ይባላል።

## 2.4. ገኔ ጌዛ (አዲስ ቦርዴ)

ገኔ ጌዛ አዲስ ቦርዴ እንደማለት ነው። አመት በአል የሚባለው ከታህሳስ 30 ጀምሮ እስከ ጥር አጋማሽ ነው። ማንኛውም የፃ/ራ ህዝብ ደሀ ሀብታም ሳይል ያከብረዋል። ገኔ ጌዛ የእርሻ ስራ ከጅምሩ እስከ መጨረሻው የሚጠይቀውን ውጣ ውረድ አልፎ ምርቱ ጎተራ ገብቶ የሚከበር በአል በመሆኑ "በአሉ ባለው ላይ መጣ እንጂ ምንም ይዞ አይመጣም ይባላል"[19]። በዚህ አመታዊ በአል የተጣላ ታርቆ ዘመድ የሚጠያየቅበትና ከአዲስ ጤፍ የተዘጋጀ ምግብ የሚበላበት ነው። አዲስ ቦርዴ የተባለው ከዚያ በፊት የተመረተው ምርት ከቤት ውስጥ ተጠናቆ አልቆ ከታህሳስ 30 ጀምሮ አዲሱ ምርት የሚጀመርበት በመሆኑ ነው። ድግሱ ሳይደገስ አዲስ የገባ ጤፍ አይበላም። ከድግሱ በኋላ አዲሱን ጤፍ እንደፈለጉ አድርገው ማዘጋጀትና መብላት ይችላሉ።

የገኔ ጌዛ ድግስ የህዝቡ ብቻ ሳይሆን ኤቃም ደግሶ የእርሻ ስራውን ለሰሩለት እንዲሁም በአካባቢው ለሚገኙ ሰዎች ግብዣ የሚያደርግበት ነው። የፃ/ራ ህዝብ በተለይ ዘመዳሞች በዚህ አዲስ ጤፍ መቅመሻ ወቅት በየቤታቸው በመጠራራት የአዲሱን ጤፍ ቦርዴ ይጠጣሉ። ከብት ያርዳሉ፤ ስጋውን ይበላሉ። ይህ በፃ/ራ ህዝብ ዘንድ ትልቁ አመታዊ በአል የዘመድ አዝማድ መጠያየቂያ መገባበዣ ወቅት ነው።

ጤፍ የሚዘራው ከሀምሌ አጋማሽ ጀምሮ ነው። ኤቀትሳዎች ሳይዘሩ ሌላ ሰው አይዘራም። ኤቀትሳ ጦር ይዞ የሚዘራበት ማሳ ውስጥ ቆሞ የሪዶንቲን በመለመን "እኔ መሬቱን ከአያቴ ከቅድመ አያቴ የተሰጠኝን ጠብቄ ቆይቻለሁ" ብሎ ለዘር ከተዘጋጀው ጤፍ ላይ በእጁ ዘግኖ

[19] ቃለመጠይቅ፣ አቶ ሺንደሚሪ አሸቱ፣ 2/4/2010ዓ.ም።

ለሚዘራው ሰው ይሰጣል[20]። ኤቀትሳው መርቆ የራሱን የእርሻ ዘር ማዘራት እስከሚጀምር ሌላው ህዝብ የሚጠብቅበት ምክንያት ድርቅ ሆኖ ዝናብ ሲጠፋ ወይም ዝናብ በዝቶ ለማረስ አላመች ሲል ዝናብ እንዲቆም ወይም እንዲዘንብ የሚለምነው ኤቀትሳ ነው ተብሎ ስለሚታመን ነው። የኤቀትሳ ማሳ በተዘራ ማግስት ሌላውም ህዝብ መዝራት ይችላል። ኤቀትሳዎች ዘር መዝራቱን መርቀው ያስጀምሩ እንጂ ስራቸውን የሚሰሩት ቤተሰቦቻቸው ወይም ፈቃደኛ የሆኑ የእምነቱ ተከታዮች በተለይ ቡርገሮች ናቸው። ጤፉ ደርሶ ለነቀላ ሲወጣ መጀመሪያ የኤቀትሳው ጤፍ መነቀል አለበት። ሌላው ህዝብ የኤቀትሳው ማሳ መነቀል በጀመረ ማግስት መንቀል ይችላል።

አንድ ሰው በአንደኛው የጤፍ ማሳው ውስጥ ለገኔ ጌዛና ለኤቃ ብሎ ማሳው መካከል ለይቶ ምልክት በማድረግ ጤፍ ሲዘራም ሆነ ሲነቀል መጀመሪያ ይዘራል፤ መጀመሪያ ይነቀላል። አንድ ሰው ይህን ለኤቀትሳ ግብር የሚሰጠውን ከአንድ እቅፍ የማይበልጥ ጤፍ ሳይነቅል ሌላውን ጤፍ ወይም የሌላውን ሰው ማሳ ጤፍ ነቀላ ለማገዝ አይሄድም። ለኤቀትስ ተብሎ የተዘራው እንደ አጋጣሚ ፍሬ ባያፈራ ከሌላው ጤፍ ላይ አስቀድሞ በመንቀል ለኤቀትሳ ይሰጣል። ለኤቀትሳ የሚሰጠው አንድ እቅፍ ጤፍ ሲሆን እያንዳንዱ ሰው ይህንን ጤፍ ቀድሞ ነቅሎ በቤቱ ደጃፍ ለጤፍ መስቀያ በተዘጋጀ እንጨት ላይ ይሰቅላል[21]። የኤቃው አገልጋዮች በየቤቱ እየዞሩ ይህንን ጤፍ ይሰበስባሉ።

ኤቃው አገልጋዮቹ ይህንን ጤፍ እንዲሰበስቡ ሲያዝ፤ ለምሳሌ ቦንገትስ ቡርገሮቹን ሲያዝ "ለገረመንዞ የሚገባውን ጤፍ ሰብስብ" በማለት ነው።

ቦንገትስም የተሰበሰበው ጤፍ ሲደርሰው "የመጣውን ለገረመንዞ አካፍዬ ስጥቻለሁ[22] የቀረው

---

[20] የኤቃን የእርሻ ስራ የሚሰሩት በአብዛኛው ቡርገሮች (አገልጋዮች) እንዲሁም ፈቃደኛ የሆኑ የትውፊታዊ እምነቱ ተከታዮች ናቸው። ኤቃዎች በየአካባቢያቸው ዘር ሲጀመር ለማስጀመር ለምርቃት እንጂ ሙሉውን የእርሻ ማሳቸውን ይዘራሉ ወይም ያጭዳሉ ማለት አይደለም። ቃለመጠይቅ፣ አቶ ጴጤ ጋይደብ፣ 11/03/010 ዓ.ም።

[21]ጤፍ የሚሰቀለው ለኤቃ የሚሰጠው ብቻ ሳይሆን ማንኛውም ጤፍ ተነቅሎ ከመውቃቱ በፊት እንጨት ላይ ፍሬው እንዳይረግፍ አርጎ ይሰቅለዋል እንጂ መከመር የተለመደ አይደለም።

[22] ቀደም ሲል ገረመንጆ የሚባል ሁሉም ኤቀትሳ የበላያቸው አድርገው በአመት አንዴ ግብር የሚያስገቡለት ኤቀትሳ ነበረ። ሆኖም ከስድስት አመት በፊት በመሞቱና የሚተካው ስላልነበረ ይህ ተቋርጧል። ኤቀትሳ በየአመቱ ከበላዩ ላለ ኤቃ ግብር ያስገባል። ኤቃዎች በየአመቱ ለመንፈሱ የሚያቀርቡትን ግብር ቢያስታጉሉ እህል በወቅቱ አይደርስም። ልጆች ይታመማሉ። ሰው ጤና አይኖረውም ተብሎ ይታመናል። አመታዊ ግብር በአመት አንድ ጊዜ በአካል ኤቃው ባለበት የየጎሳው ኤቃ ለዋናው ኤቃ የሚያስገቡበት ነው። ግብሩ ጥቁር መልክ ግንባሩ ላይ ነጭ ያለው ወይፈን ነው። ኤቃው የዚህ አይነት መልክ ያለው ወይፈን ወይም በሬ ከሌለው ቀድሞ ጥጃውን ገዝቶ ያሳድጋል። ግብር የሚያስገቡት በገንዘባቸው የገዙትን ወይም ያረቡትን እንጂ በስእለት የትውፊታዊ እምነቱ ተከታዮች የሰጡት ቢኖርም ለበላይ ኤቃ አይሰጥም።አንድ ኤቃ ግብር ከማቅረቡ በፊት ለቀናት የሚታቀባቸው ድርጊቶች አሉ። ለምሳሌ ከሚስቱ መገናኘ አንዱ ነው።ወይፈኑን የሚነዱት ጤፍ የሚሸከሙት ቡርገዦ ሲሆን ኤቃው ጦሩን ብቻ ይዞ ይሄዳል። ሌሎችም አቻ የሚሆኑ ኤቃዎች በተመሳሳይ ቀን ይሄዳሉ። ግብር የሚወሰድለት ታላቁ ኤቃ ግብር ላመጡለት ኤቃዎችና አገልጋዮቻቸው ራሳቸው ኤቃዎች ከወሰዱት የግብር ከብት መካከል ተመርቆ ታርዶላቸው ይስተናገዳሉ። አንድ ኤቃ ግብር አስገብቶ ሲመለስ ባዶ እጅ አይመለስም። ይዞ ከሄደው ውጭ የበላዩ ኤቃ ጦር ይሰጠዋል። አንድ ኤቃ ለበላዩ ኤቃ አመታዊ ግብር አስገብቶ እንደተመለሰ ወደ ሚስቱ አይሄድም። ለሰባት ቀን በአምልኮ ስፍራው ይቀመጣል። በዚህ ሰባት ቀን ቆይታው አማኞቹ አስቀድመው ተዘጋጅተው ይጠብቁታል። በስእለት ከመጣለት ከብት መካከል ይታረዳልናይበላሉ። ቦርዴና ቡናም ይጠጣል። ማታ እሳት እያነደዱ ተከታዮቹ አብረው ይቆያሉ። ኤቃው ለሀገሩ ለህዝቡ በረከት እንዲሆን ይመርቃል። አማኞቹ የነደደውን እንጨት አመዱን ግንባራቸው ላይ ይቀባሉ። ቃለመጠይቅ፣ አቶ ታመነ ተሰማ(ኤቀትሳ)፣1/3/2012ዓ.ም

ይበርክት" ብሎ ይመርቃል። በቆሎና ጤፍ ሲደርስ መጀመሪያ ለኤቀትሳ የሚሰጠው የቀረው በረከት እንዲኖረው፣ የጤና ምግብ እንዲሆን፣ ሀገር ሰላም እንዲሆን በሽታ እንዲጠፋ ኤቃትሳው የሪዶንቲን እንዲለምን እና ህዝቡን እንዲመርቅ ነው።

ኤቀትሳው ለዘመድ አዝማዱ በቤቱ ከራሱ ማሳ ላይ የተነቀለውን ጤፍ ቦርዴ እና የከብት ስጋ ይጋብዛል። በኤቀትሳ ቤት የሚዘጋጀው ቦርዴ ጤፉ የሚፈጭና የሚዘጋጀው በራሱ ቤት ነው። ጤፍ የምትፈጨው የወር አበባ ያላየች ልጃገረድ ተመርጣ ካለችበት መጥታ ነው። ጤፉን የምትፈጨው ልጅ ሳትጨርስ ወደ ቤቷ ሄዳ ተመልሳ ለመምጣት አይነምድር እንዳትረግጥ ተጠንቅቃ ነው[23]። ይህ ቦርዴ የሚዘጋጀው የኤቃውን ጤፍና ሌላም ሰብል በማረስ በማረም እንዲሁም በመንቀል የተሳተፉ ቡርገሮች ዘመዶቹ እንዲሁም በፈቃዳቸው ለሰሩ ለኤቃ ትውፊታዊ እምነት ተከታዮች ነው። በተጨማሪም ኤቀትሳው የአካባቢውን ሰው (ለእሱ የሚገብሩትን) ሊጋብዝ ይችላል።

የገነኔዛ ዋናው በአል የሚከበረው ታህሳስ ሰላሳ ሲሆን ተጋባዦቹ በዋዜማው ታህሳስ 29 ኤቃው ዘንድ ገብተው ያድራሉ። ቡና የምታፈላው የኤቃው ሚስት በዚያን እለት ንጹህ ካልሆነች ልጃገረድ ተፈልጋ ቡናውን ታፈላለች። ኤቀትሳው ቦርዴውን በቅል በመያዝ "ይህን የሰጠህን አምላክ፣ ይህን ህዝብ ባርክ፣ ጠብቀው፣ እህል ይብቀል፣ በሽታ ይጥፋ፣ ከብቱ ሰላም ይሁን፣ ሀገሩን ሰላም አድርግ፣ መንግስትን ጠብቅ ብሎ መርቆ ሲጨርስ ከቦርዴው ፉት ብሎ በአራቱም አቅጣጫ እንትፍ እንትፍ ብሎ የቀረውን ምሰሶው ሥር ያስቀምጣል። ምሰሶ ስር ያስቀመጠውን ቡርገሮ በዚያ ለተገኙት በተራ እንዲቀምሱ ይሰጣል። በድግሱ የታደመው በሙሉ እየተቀባበለ ይቀምሳል። ከዚህ በኋላ የተዘጋጀው ምግብም መጠጥም ቀርቦ ይበላል፤ ይጠጣል።

ኤቀትሳም ሆነ ሌላው ህዝብ ለገኔ ጌዛ የሚበላና የሚጠጣውን ከጤፍ ብቻ ያዘጋጃል። ማር በብዛት ቢኖርም ገነኔዛ የጤፍ እንጂ የማር መጠጥ አይዘጋጅም። በጤፍ ከሚዘጋጀው ምግብና መጠጥ በተጨማሪ ስጋ ይበላል። አቅሙ የቻለ ለራሱ ቤተሰብ ብቻ ከብት ያርዳል። በግሉ ማረድ ያልቻለ ከዘመዶቹ ጋር ተቀናጅቶ በጋራ(ቅርጫ) በሬ አርደው ስጋውን ይከፋፈላሉ። የሚታረደው ከብት ከተቻለ በሬ ወይም ወይፈን ካልተቻለ ጊደር (ላም አትታረድም) ሲሆን በጣም ደሃ ከሆነ ዶሮ ያርዳል።

ለድግሱ ጥሪ ሲደረግ በእለቱ ጠዋት "ቡና ጠጡ" ይባላል። የመጀመሪያው ጋባዥ ታላቅ የሆነ ቀድሞ አዘጋጅቶ ከጠራ ቅድሚያ ይሰጠዋል። ግን ቀዳሚው የቦርዴውን እህል ቀድሞ የፈጨ ወይም ያዘጋጀ ቤተሰብ ነው። ምክንያቱም ቦርዴው ተሰርቶ ለመጠጥ ለመድረስ አንድ ሳምንት ይፈጃል።

[23]የኤቃን ጤፍ የምትፈጨው የምትጠነቀቅበት ምክንያት በመንገዱ ላይ በአጋጣሚ አይነ ምድር እንዳትረግጥ ነው። ድንገት ብትረግጥ ወደ ኤቃ ግቢ ከመግባቷ በፊት እግሯን በግራዋ መታጠብ፣እና ማንጻት አለባት።

ዘመድ አዝማድ ይሰበሰባል ቦርዴ ይቀርባል። ስጋውን ወጣት ወንድ ልጆች ለሚጋበዘው ዘመድ አዝማድ እንዲዳረስ ቆራርጠው የሚበስለውን በነደደ እሳት ላይ በመጥበስ ጥሬውን ለብቻ ለስጋ ዘመድ ተጋባዦች ያዳርሳሉ። ጎረቤታሞች ይገባበዛሉ ሆኖም ለጎረቤት መስተንግዶ ስጋ አይቀርብም። የሚቀርበው ቦርዴ እንዲሁም የጤፍ ዳቦ በወጥ (በደቃቅ ክክ ኑጭና ቀይ ሽንኩርት፣ ቃሪያ፣ ቅቤና በመሳሰሉት ማጣፈጫ የተሰራ) ነው። ለማንኛውም ሰው ቦርዴ ሲጠጣ በደንብ እንዲጠጣ ቃሪያ ተደቁሶ አብሮ ይቀርባል። ቡና ይፈላል። ከታህሳስ 30 ጀምሮ እንደዘመድ ብዛት(እንደሚጠራራው ሰው ብዛት) ከሳምንት በላይ ሊቆይ ይችላል። በመጀመሪያው እለት በታህሳስ 30 ከተመረቀና ድግሱ ከተጀመረ በኋላ እየዞሩ መብላት እንጂ መጨረሻው ቀን አይወሰንም።

በፃራ ህዝብ ትውፊታዊ እምነት ውስጥ ሌላው የሚከበርና የሚፈራ መንፈስ ቆሉ ነው።

**2.5 ቆሉ**

ቆሉ ጫካ(ደን) ውስጥ የሚኖር መንፈስ ነው። ቆሉ ለሰው አይታይም፣ ከሰዎች መኖሪያ ራቅ ባሉ ደኖች ውስጥ ይኖራል። ቆሉ ከሰዎች የሚፈልገው በፃራ ምድር ከበቀሉ እና የሰው ልጅ ለምግብነት ከሚጠቀማቸው አዝእርቶች መካከል ማንም ሳይቀምስ የመጀመሪያው እንዲሰጠው ነው። በአመት አዝመራ በተለይ እሸቱ ሲደርሰው ከሚሰጠው በተጨማሪ በየእለቱ እያንዳንዱ አባ ወራ በየእለቱ ምግብም ሆነ መጠጥ ከመቅመሱ በፊት በመሬት ላይ ምግቡን በመጣል መጠጡን በመርጨት ድርሻውን እንዲሰጠው ነው። ይህ ካልሆነ ግን ቆሉ በአካል ሳይሆን በቅጣቱ በተለያየ መንገድ ይገለጻል። የፃራ ህዝብ በሚኖርባቸው ከመኖሪያ ቤት ራቅ ብለው በሚገኙ ደኖች ቆሉ ይኖራል ተብሎ ይታመናል። ቆሉ ያለበት ደን ውስጥ በአብዛኛው የኤቃ መሪዎች የማምለኪያ ስፍራቸውን ኤቀ ኬታ ይሰሩበታል። ለመብረቅ የስእለት የግብር ከብት ይታረድበታል። ማንም ሰው ያለበቂ ምክንያት ወደእነዚህ ደኖች አይሄድም[24]። ህጻንም ቢሆን ቆሉ ያለበት ጫካ ውስጥ አይገባም። ምክንያቱም ቆሉ ሴት ወንድ ህጻን አዋቂ ሳይል በዚያው ደን ውስጥ ያስቀራል ተብሎ ይታመናል። ቆሉ ያለበት ደን ውስጥ ዛፍ አይቆረጥም። ዛፉ በራሱ ቢወድቅ እንኳን እዚያው ይበሰብሳል። ቆሉ ያለበት ደን ቢመነጠር ሀገሩ ሰላም አይሆንም፤ የተመነጠረው ቦታም እህል ቢዘራ አይበቅልበትም። "ደን መመንጠር ብንፈልግም እሺ ብሎ አይመነጠርም። ለምሳሌ ከኃይለስላሴ ጀምሮ ይህ ፊት ለፊታችን ያለው ቦታ(ጎሲ ይባላል)ወንዝም አለው፣ ለመመንጠር ተሞክሮ አልመነጠር ብሎ እስከዛሬ አለ"።[25]

ቆሉ እንደ ኤቃ በግለሰብ ላይ የሚያድር መንፈስ አይደለም። ማንኛውም ሰው ምግብ ሊመገብ ሲል ከመቅመሱ በፊት ከአናቱ መጣል የሚጠጣ ሲሆን ማፍሰስ ቆሉ ከሚፈልጋቸው አንዱ ነው። ሰብል ሲደርስ በቆሎ እና ማሽላ እሸት ከመቀመሱ በፊት መጀመሪያ ለቆሉ ይሰጣል። ህጻናት ጭምር ለቆሉ ሳይሰጥ ተሳስተው እሸት እንኳን እንዳይቀምሱ ይነገራቸዋል፤ ይጠበቃሉ። አንድ የፃራ ብሄረሰብ አባል የትውፊታዊ እምነት ተከታይ በተለያየ ምክንያት ከሚኖርበት አካባቢ ርቆ

[24] በቂ ምክንያት ከሚባሉት ለምሳሌ መድሀኒት ፍለጋ ሊገባ ይችላል።
[25] ቃለመጠይቅ፣ አቶ ጎርጊስ ቤልዳሚር፣ 10/ 9 /2011ዓ.ም።

ሄዶ ምግብ ቢበላ ከሚበላውም ሆነ ከሚጠጣው ላይ ለቆሉ መስጠት የለበትም። ምክንያቱም ቆሉ አሁን የፃራ ህዝብ በሚኖርበት ምድር በተለይም በሚኖርበት አካባቢ እንጂ በሰው ሀገር የለም። በሌላ ሀገር ወይም አካባቢ ያለ ቆሉ በዚያው አካባቢ የሚኖሩት ሰዎች ቆሉ ነው። አንድ ሰው በአካባቢው እንጂ በሌላ አካባቢ ሄዶ በዚያ ለሚገኝ ቆሉ እሸትም ሆነ ምግብ መጠጥ ቢሰጥ በቆሉ ይቀጣል። “የፃራ ህዝብ ቆሉ ያለው የፃራ ህዝብ ባለበት ነው”።[26]

ለቆሉ የማይሰጡ የምግብ አይነቶች በቅርብ ጊዜ ከሌላ ቦታ የወሰዷቸው አዝእርትችና ፍራፍሬዎች ናቸው። ለምሳሌ አቦካዶ በአካባቢው በተለይም በመኖሪያ ቤት አካባቢ አፍርቶ ልጆች ይበሉታል ሆኖም ለቆሉ አይሰጥም። ምክንያቱም ይህ በእኛ ምድር ላይ አልበቀለም። ለአያቶቻችን እና ለቅድመ አያቶቻችን የተሰጠ ዘር አይደለም በሚል ነው።

በቆሎና ማሽላ እሸቱ ሲደርስ እያንዳንዱ የእምነቱ ተከታይ ጫካ ሆኖ ገደላማ የሆነበት ቦታ እሸት እና ለማገዶ የሚሆን እንጨት በመያዝ ይሰባሰባሉ። እያንዳንዱ ቤተሰብ ይዞ የሄደውን እሸት ለምሳሌ በቆሎ ከሆነ ጡብሰው ማሽላውን በእጅ ይዘው እሳት ላይ በመለብለብ፤ “ይህንን ማሽላና በቆሎ ጠብቀህ በሰላም ያደረስክ ቆሉ እኛ ከሙብላታችን በፊት ብላ” በማለት መጀመሪያ የበሰለው ይበተናል። ከተበተነ በኋላ የመጣው ሰው በሙሉ ከበሰለው በቆሎ በልቶ ወደየቤቱ ይሄዳል። እሸት ደርሶ በዚህ መልኩ ለቆሉ ሳይሰጡ ከቀመሱ ወይም ከበሉ ቆሉ ያጠፉቸዋል ወይም በህይወት ወስዶ ጫካ ውስጥ ይደብቃል፤ ይገድላቸዋል። ስለዚህ ያገዳ እህል እሸቱ እንደደረሰ ከቤተሰቡ አባል አባት ለቆሉ ይሰጣል።በአመት አንዴ የአንድ አካባቢ ሰው በሰፈሩ ተሰባስቦ ከሚሰጠው በተጨማሪ የጓሮ አትክልት ሲደርስም መጀመሪያ ትንሽ ቆርጦ ወይም ነቅሎ ቆሉ አንተም ቅመስ ብሎ መጀመሪያ ይወረውራል።

“መሬታችን ላይ የበቀለን አባቶቻችን ሲበሉ የኖሩትን ሁሉ ሲደርስ እንሰጣለን”።[27] እሸት ደርሶ ለቆሉ ተሰጥቶ ደርቆ ሲሰበሰብ ደግሞ ለኤቃ ይሰጣል። አንድ ሰው ለምሳሌ በቆሎ እንደ ደረሰ ከነአገዳው ሽፋኑን ሳይሸለቅቅ አንድ ሸክም ለኤቃ ይሰጣል። የቆሉ መልእክተኛ ለሆነው ኤቀትሳ የደረሰ በቆሎ ወይም ሌላ የሚሰጥ ሰው ንጹህ መሆን አለበት። ድንገት ከሚስቱ ተገናኝቶ ንጹህ ሳይሆን ቀርቶ የግድ መስጠት ካለበት፤ ከእህሉ ጋር አብሮ አንገቱ ላይ ከሚያደርገው ጨሌ አራት ፍሬ አውጥቶ በክር አስሮ ይሰጣል። ኤቀትሳም ለምሳሌ “የበሉትን አታጥፋ፣ አይሙቱ” በማለት ይመርቀዋል። አብሮ የሰጠው ጨሌ ካለም ከመኖርያ ቤቱ ጀርባ በስተቀኝ ግርግዳ ላይ ወይም እንጨት ላይ ይሰቅለዋል።

የደረሰን እህል ለቆሉ ሳይሰጡ ከበሉ ቤተሰቦች መካከል አንድ ሰው ልጅም ሆነ አዋቂ ሴትም ሆነች ወንድ ቆሉ ወስዶ እሱ ባለበት ደን ውስጥ ለሰው እንዳይታይ አድርጎ ይደብቀዋል። ቆሉ ተቆጥቶ

[26]ቃለመጠይቅ፣ ወ/ሮ ኦትሬ ደንበጃ፣ 29/3/2010 ዓ.ም።

[27]ቃለመጠይቅ፣ አቶ ኢርታንቆ ለገሰ፣ 30/8/2010 ዓ.ም።

ሰው ከወሰደ የተወሰኑ ሰዎች ህዝቡን ወክለው ኤቀትሳ ዘንድ ፍየል ይዘው በመሄድ ቆሉ የወሰደውን እንዲመልስ ይለምናሉ። ለልመናው ጥቁር ዶሮ፣ ፍየል፣ ጥቁር አዝሙድ፣ ነጭ ሽንኩርት እና እሳት ያስፈልጋል። እነዚህ የተመረጡበት ምክንያት ነጭ ሽንኩርት በጣም ሽታ ስላለው፣ ጥቁር አዝሙድ ከቅመም ሁሉ ስለሚወደድ፣ ዶሮ ከሌላው ይልቅ ለሰው ቅርብ በመሆኑ መልኩ ጥቁር መሆኑ እንደሰው መልክ የሚታሰብ ስለሆነ ቆሉ የወሰደውን ሰው ሲመልስ ዶሮው ምትክ ይሆናል ተብሎ ነው። የዶሮ ፆታ በጠፋው ሰው ይወሰናል። ቆሉ የወሰደው ወንድ ከሆነ ወንድ ዶሮ፣ ሴት ከሆነች ሴት ዶሮ ነው። ፍየል የተፈለገበት ምክንያት ቆሉ ፍየል አይወድም። ስለዚህ ፍየሉን ቆሉ ያለበት ድረስ በመውሰድ እሳት በማንደድ አስፈላጊ የሆነው ሁሉ ከተዘጋጀ በኋላ የፍየሉን ጆሮ ይቆነጥጡታል። ፍየሉ ሲቆነጠት ይጮሀል በዚህን ጊዜ ቆሉ የሚጠላውን የፍየል ድምጽ ሲሰማ አንድ ሰው ደግሞ የጠፋውን ሰው ስም ይጠራል በዚህን ወቅት በቆሉ የተያዘው ካለበት ወጥቶ ለሰው ይታያል። በቆሉ ተወስዳ ከሁለት አመት በኋላ ከላይ የተባሉትን በማድረግ የተመለሰች ልጅ አለችኝ የሚሉት አባት ሲሆን አይተናል ያሉት የአካባቢው ሰዎች ጭምር እንደሚከተለው ይተርካሉ።

> የ12 አመት ልጅ በ2001 ዓ.ም ቆሉ ወሰደቻት። ቆሉ ወስዳ ሁለት አመት እዚያው ደን ውስጥ ኖረች።የልጅቷ ቤተሰብ ልጃቸው የት እንደጠፋች ኤቃ ጠየቁ። ኤቃው ለረዥም ግዜ በተደጋጋሚ የሪዶንቲን በመለመን አንድ ቀን ተገለፀለት። ኤቀትሳው ኤቄ ኬታ በመሆን ከመንፈሱ ተገናኝቶ ልጅቱ የት እንዳለች ለማግኘት ምን ምን ማድረግ እንዳለባቸው ለቡርገ ተናገረ። ቅመማ ቅመም ጥቁር ዶሮ ፍየል ይዛችሁ 'ገምዛ ብራ' የሚባለው ተራራ ዘንድ ሄዳችሁ አቅርቡ ብሎ አዘዘ። እነሱም የተባሉትን አድርገው ጨርሰው ልጅቱን በስሟ ሲጠሯት ወደ እነሱ መጣች። ከቤተሰቧ በተለየች ሁለት አመቷ በ2003 ዓ.ም ተገኘች። ልጅቱ አሁን አግብታ ወልዳለች። የሚደረገውን አድርጉ ብለው መርቀው ያስወጧት ኤቀትሳው አቶ ታመነ ናቸው።[28]

ለቆሉ ስእለት ይሰጣል። ለቆሉ ከሚሳሉት ስእለት መካከል በቆሎ አንዱ ነው። የበቆሎ እርሻ ሲጀምሩ "ይህ በቆሎ ከደረሰ ለቆሉ እሰጣለሁ" ብለው ቃል ይገባሉ። ቢቃላቸው መሠረት እህል ሲደርስ የተሳሉትን ይዘው ኤቀትሳው ዘንድ ይሄዳሉ። ለቆሉ ለመጣ ስእለት ኤቀትሳው የሚመርቀው "የጥቁር ዶሮ ስጋ ብላ"[29] ብሎ ነው። ለቆሉ እርድ ይታረዳል። ዶሮ ተራራ ላይ የሚቀርብ የቆሉ መስዋእት ነው። በአጠቃላይ ጥቁር ዶሮ፣ መጀመሪያ የደረሰ የቆሎና ማሽላ እሸት የቆሉ መስዋዕት የሚሆኑ ናቸው።

---

[28] ቃለመጠይቅ፣ አቶ ሺንደሚሪ እሸቱ፣ 2/4/2010 ዓ.ም። እንዲሁም የቡድን ውይይት፤ አቶ ጴጤ ጋይደብ፣ ወ/ሮ ሙላ ሙልጌቲ፣ ወ/ሮ ኦትሬ ደንብጃ፣ ወ/ሮ ገነት ቡሻ፣ አቶ ደንበላሽ ሺንደመር (ቡርዥ) እና አቶ ኢርታንቆ ለገሰ 4/04/2012።

[29] ቃለመጠይቅ፣ አቶ ታመነ ተሰማ(ኤቀትሳ)፣15/4/2010ዓ.ም

## 2.6 ገራትሳ፣ ቡርዠትሳ፣ ከራትሳ እና ገራ

በፃራ ህዝብ ትውፊታዊ እምነት በኤቃ ማመኑ እንዳለ ሆኖ የተለያዩ ግለሰቦች ኤቃን በማስፈቀድ እንዲሁም የተለያዩ ቁሶችን ከጎሳቸው ወይም ከእናት ከአባታቸው በወረሱት መንፈስ የማወቅ የማዳን ሀይል እንዳላቸው ይታመናል። እነዚህ ግለሰቦች ለማህበረሰቡ የሚሰጡት አገልግሎት ህመምን የማዳን፣ ርኩሰትን የማንጻት ትንቢት የመናገር እንዲሁም የተደበቀን ያውቃሉ ተብሎ የሚታመንባቸው ወንዶችም ሴቶችም ናቸው። መጠሪያቸውም ገራትሳ፣ ቡርዠትሳ፣ ከራትሳና ገራ ይባላሉ። በአጭሩ አራቱን እንደሚከተለው እንመለከታለን።

**ገራትሳ** የሚባሉት ሰው የቸገረውን ሲጠይቃቸው ስለተጠየቀው ሰው በአካል ሳያዩት በሌለበት ስለእሱ የሚያውቁ ትንቢት የሚናገሩ ናቸው። የገራትሳን ተግባር እንዲሰሩ በኤቀትሳ የተፈቀደላቸው ሴቶች ሲሆኑ ለተጠየቁት ምላሽ የሚሰጡት የፈሰሰ ውሃ በማንበብ ነው። አንዲት ሴት ወደገራትሳ ተግባር ከመግባቷ አስቀድማ ገራትሳ መሆኗን የምታውቀው በራእይ ነው። ገራትሳ መሆኗን በራእይ ያየች ሴት የእሷ ጎሳ ለሆነ የኤቃ መሪ ሄዳ ትናገራለች። ራእዩን እራሷም ሆነች ቤተሰቧ ወይም ሌላ ሰው መፍታት ቢችልም እውቅና የሚሰጣት ኤቃ ነው። ስለዚህ ራእይ ያየችው ሴት ለኤቀትሳ ትነግረዋለች። ኤቀትሳ የሰዎችን ችግር ሰምታ የተገለጸላትን እንድትናገር መርቆ ፈቃድ ይሰጣታል። ከተመረቀች በኋላ አገልግሎቷን ፈልገው ለሚመጡ ሰዎች አገልግሎት ትሰጣለች።

ገራትሳ የሆኑ ሴቶች እንደኤቀትሳ ኤቀ ኬታ ወይም የተለየ ቤት የላቸውም። አንዲት ገራትሳ እንደማንኛዋም ሴት የማህበረሰቡን ባህላዊ እሴቶች ጠብቃ በቤቷ ትኖራለች። ለጉዳይ የሄደ ግለሰብም ገራትሳዋ ቤት በመሄድ ይጠይቃል። ገራትሳ የሆነች ሴት ሌላ ሰው በሌለችበት የሚፈጽመውን ተግባር የምታውቀው ውሃ በማየት ነው። በትልቅ ቅል ውሀ ቀድታ፤ በትንሽ ቅል እየቀነሰች መሬት ላይ በመርጨት የተለያየ ቦታ ላይ ውሀውን በማንጠባጠብ እያየች ለተጠየቀችው ምላሽ ትሰጣለች። ሌላ ሰው ግን የፈሰሰው ውሃ ላይ ምንም የተለየ ነገር አያይም። "የጠየቅናትን ወደፊት የሚገጥመንን ጭምር ትነግረናለች።"[30] የታመመ ሰው ከሆነና በውሃ ስታይ የሚሞት ከሆነ ገንዘብ አትቀበልም። የታመመው ሰው የሚድን ከሆነ ግን ገንዘብ ትቀበላለች። በዚህ መልኩ የተሰጣትን ገንዘብ አጠራቅማ በቅድሚያ ከገንዘቡ ቀንሳ ለኤቀትሳ ሰጥታ የተረፈውን ገንዘብ ትጠቀምበታለች።

**ቡርዠትሳ** የሚባለው ወንድ ሲሆን በተለያየ ስህተት ወይም ጥፋት ምክንያት የረከሰን ሰው የማንጻት (ለምሳሌ ዝሙት የፈጸመ) እንዲሁም ተላላፊ በሽታ ሲገባ በሽታው ከአካባቢያቸው እንዲጠፋ የማድረግ ሀይል ያለው ግለሰብ ነው። ቡርዠትሳ የሚሆነው ከፃራ ጎሳዎች መካከል የሀርከትሳ ጎሳ አባል ነው። ቡርዠትሳ እንደ ኤቀትሳ በየጎሳው ስለማይኖር ሲፈለግ ለምሳሌ በአንድ መንደር ተላላፊ በሽታ ቢገባ በሽታው እንዲወጣ ወይም እንዲጠፋ የሪዶንቲን ለመለመን ይሄዳል።

[30] ቃለመጠይቅ፣ ወ/ሮ ሙላ ሙልጌቲ፣ 6/4/2010ዓ.ም።

ሁለት ሶስት ቀን በእግሩ ተጉዞ የተፈለገበት ቦታ ድረስ መሄዱ የግድ ሲሆን የሚፈልጉት ሰዎች ያለበት ድረስ በመሄድ ወደሚፈልጉበት ቦታ እንዲመጣ የመጠየቅ ግዴታ አለባቸው።

ቡርዠትሳ በሽታ ከአካባቢው እንዲጠፋ ወይም የረከሰን ሰው የሚያነጻው እርጥብ እንጨት ሰብቆ እሳት በማውጣት ነው። እሳት የሚያወጣው ከማንኛውም እንጨት ሳይሆን በበረሃ የሚገኝ "ኔጤራ" ተብሎ ከሚጠራ እንጨት ነው። የእንጨቱ ውፍረት የእስክሪብቶ ቀፎ ያህል ሲሆን የሚነጻ ሰው ሲኖር ወይም ተላላፊ በሽታ በአካባቢው ገብቶ ከሆነ ቡርዠትሳ ጫካ ገብቶ ፈልጎ ኔጤራ የተባለውን እንጨት ያመጣል። ወይም አስቀድሞ በሀርከትሳ ፈቃድ ተፈልጎ መጥቶ በመኖሪያ ቤት የውጭ ግርግዳ ላይ (እቤት ውስጥ አይገባም) ሊቀመጥ ይችላል። ኔጤራ የወር አበባ ያለባት ሴት አትነካውም።

ቡርዠትሳ በማለዳ አስራ አንድ ሰአት ተኩል አካባቢ ተነስቶ እንጨቱን አሽቶ እሳት ለማውጣት መጀመሪያ የሪዶንቲን ይለምናል። "አንተ ፈጣሪ ይህችን እንጨት የፈጠርካት አንተ ነህ። እኛ ዘንድ በሽታ ገብቷል። እኛ በሽታውን ለመከላከል አቅም የለንም፤ አንተ ይህንን እሳት ከዚህ እንጨት እንዳወጣህ በሽታውንም ከቤታችን ከአካባቢያችን ከሀገራችን አውጣ"[31] ብሎ ይለምናል። በቅድሚያ በእንጨቷ ውፍረት ልክ መሬት ላይ ትንሽ ጉርጓድ ይዘጋጃል። እንጨቱ ጉርጓድ ውስጥ ገብቶ ከጉርጓዱ በላይ ቢላ በማድረግ ከላይ በእጁ ይሰብቃል። ቡርዠትሳ ኔጤራን ሲሰብቅ ከመሬት በኩል ባለው እርጥብ እንጨት እሳት ይወጣል። "ቡርዠትሳ ለዚህ ተብሎ ስልጣን የተሰጠው እንዲሁም እንጨቱ የክብር እንጨት ስለሆነ እንጂ ከእርጥብ እንጨት እሳት አይወጣም"[32]። ቡርዠትሳ እሳቱን ካወጣ በኋላ እሳቱን በአራቱም መአዘን በማሳየት "የሞተው ሞቷል አይመለስም፤ ቀሪው ሰው እንዲተርፍ በሽታው በዚህ መልክ እንዲጠፋ ይለምናል። ቡርዠትሳ ቀሪውን እንጨት በማሰር ኤቀትሳ በቅርብ ካለ እዚያ፣ አለዚያ ሌላ ንጹህ ቦታ ይቀመጣል። ቡርዠትሳ ስራውን ሲጨርስ ጠርተው ያመጡት ሰዎች በማስተናገድ ወደ ቤቱ ሲመለስ ገንዘብ ይሰጡታል። ቀደም ሲል ለቡርዠትሳ የሚሰጠው አራት ብር ሲሆን አንዳንዴ የአካባቢው ሰው ተባብሮ ወይፈንም ሊሰጠው ይችላል።

**ከራትሳ**፣ የሚባሉት የፍየል የዶሮ የከብት አንጀት የሚያነቡ ወንዶች ናቸው። አንጀቱን ለማንበብ ሲባል እዲነበብለት የሚፈልገው ግለሰብ ወይም ቤተሰብ ከብት በማረድ አንጀቱ እንዲነበብለት ያደርጋል። የሚታረድ ከብት ከሌለ ፍየል ከጠፋ ዶሮ ታርዶ አንጀቱ ይታያል። አንጀቱ ወጥቶ ወንፊት ወይም የእንሰት ቅጠል ላይ ይደረጋል። አንጀቱን የሚያነብ ሁለት ሶስት ከራትሳ ሊሆን ይችላል። ከራትሳዎች አብረው በመቀመጥ አንጀቱን ያነቡታል። ለምሳሌ ለዚህ ጥናት የከብት አንጀት ያስነበቡት ግለሰብ በጠና በመታመማቸው ነበር። አንጀቱ ተነቦ የተነገራቸው የህመማቸው መንስኤ የተለያዩ አራዊትን አድነው ይገድሉ ስለነበር የአራዊቱ ደም እንደሆነ ነው። ለዚህም

[31] ቃለመጠይቅ፣ ወ/ሮ ኦትሬ ደንበኛ፣ 29/3/2010 ዓ.ም።

[32] ቃለመጠይቅ፣ ወ/ሮ ኦትሬ ደንበኛ፣ 29/3/2010 ዓ.ም።

ከራትሳዎቹ የታመሙት ግለሰብ እንዲድኑ በከብት ደም ቢታጠቡ ከአራዊቱ ደም ስለሚነጹ ይፈወሳሉ የሚል የመፍትሄ ሀሳብ አቅርበው እንዳሉት ተደርጎ ከህመማቸው ድነዋል[33]።

***ገራትሳ*** ገራትሳ የሚባለው የተቸገረ ሰው ሲጠይቀው የጎሽ ቆዳ በእጁ መዳፍ ላይ በመምታት የተቸገረው ሰው የችግሩ መንስኤ ምን እንደሆነ ማየት ይችላል ተብሎ የሚታመንበት ግለሰብ ነው። ገራ የሚለው የቃሉ ትርጉም የጎሽ ቆዳ ማለት ነው። የጎሽ ቆዳ ሀምሳ ሴንቲ ሜትር ባለው መጠን አራት አምስት ቦታ ቆርጠው አንድ ላይ በማገናኘት የሚያነቡ ገራትሳ ይባላሉ። እነዚህ በጎሽ ቆዳ ስለሚጠየቁት ጉዳይ የሚናገሩት እቤታቸው ሆነው ሲሆን የቸገረው ሰው ባሉበት ሄዶ ይጠይቃል። ለዚህ አገልግሎታቸው ቀደም ሲል ሁለት ብር ከቅርብ ጊዜ ወዲህ አምስት እንዲሁም አስር ብር ይከፈላቸዋል።

### 3. ማጠቃለያ

በአጠቃላይ የፃራ ትውፊታዊ እምነት መስራች የሪዶንቲ ነው። የሪዶንቲ ሰውን ጨምሮ በምድር ላይ ያለውን ሁሉ እንደፈጠረ በትውፊታዊ እምነቱ ተከታዮች የሚታመንበት ነው። ለኤቀትሳ የእምነቱ መሪ እንዲሆን የፈቀደለት የሪዶንቲ ነው። ኤቃም በመረጠው ሰው ላይ በማደር የሪዶንቲ በፈቀደለት መሰረት ያገለግላል። ኤቃ የመረጠውና ያደረበት ግለሰብ ኤቀትሳ ይባላል። ኤቀትሳ ማዘዝ ያለበትን ያዛል፣ የሚመረቁትን ይመርቃል፣ ለሰዎች ከተለያየ ችግር እንዲጠበቁ የሪዶንቲን ይለምናል። እንዲሁም የሪዶንቲ ከፈቀደለት አኗኗር ውጭ እንዳይኖር በየእለቱ ይጠነቀቃል። የሪዶንቴ ኤቀትሳ እንዲያከብራቸው ያዘዘውን ትእዛዛት ከተላለፈ ከፍተኛ የሆነ ቅጣት ይደርስበታል ተብሎ በጽኑ ይታመናል። በፃራ እያንዳንዱ ጎሳ የየራሱ ኤቃ አለው። የየጎሳው ኤቃም እንዲሁ በስሩ በርካታ ኤቃዎችን ያዛል። እሱም እንዲሁ የበላይ ኤቃ አለው።

እያንዳንዱ ኤቃ በአካባቢው ደን ውስጥ ለሚገኝ ቆሉ በየአመቱ ከህዝቡ የተሰጠውን በቆሎ እና ማሽላ ቀንሶ ይሰጣል። ህዝቡም እንዲሁ ሲበላም ሲጠጣ ለቆሉ ከአናቱ ይጥላል። በቆሎ ማሽላ ሲደርስ የየአካባቢው ሰው ተሰባስቦ እሸቱን ለራሱና ለቤተሰቡ ሳያቀምስ ለቆሉ ያቀምሳል። በየቦታው የሚጣለውን እሸትም ሆነ ምግብና መጠጥ በአካል የማትታየው የቆሉ መንፈስ እንደምትወስድ ይታመናል። ለቆሉ ሳይሰጡ መብላት ከበሉት ቤተሰብ መካከል ቆሉ አንዱን ወስዶ በሚትኖርበት ደን ውስጥ ይውራቻዋል። በቆሉ ቅጣት ላለመቀጣት እያንዳንዱ አባ ወራ በቤቱ በቀዬው በየእለቱ ሲበላ ሲጠጣ ከአናቱ እንትፍ እንትፍ ብሎ ወይም ከሚበላው ላይ ረጭቶ አንተም ብላ ብሎ ቆሉን በበላ እና በጠጣ ቁጥር ያስታውሳል። ቆሉም ሲበላ ሲጠጣ አስቀድሞ ላቀመሰው አክብሮ፣ በረከት ጨምሮ ቤተሰቡን በሰላም ያኖራል። ስእለት የኤቃ ትውፊታዊ እምነት አካል ነው። አንድ ሰው ሲቸግረው ለማንኛውም ችግሩ ኤቃ፣ የመብረቅ አምላክ

[33] የቡድን ውይይት፡- አቶ ታመነ ተሰማ፤ አቶ ሺንደሚሪ እሸቱ፤ ወ/ሮገነት ቡሻ፤ አቶ ኬሮ በላቸው፤ ወ/ሮ ኦትሬ ደንበጃ እና አቶ አቱሞ ዶርጫዬ 10/11/2011ዓ.ም

እንዲሁም ቆሉ ችግርችንን ይፈታል ብለው በማመን ችግራቸው ሲፈታ ወይም ምኞታቸው ሲሳካ ቃል የገቡትን ስእለት ቃል ለገቡለት ይሰጣሉ።

የኤቃ ትውፊታዊ እምነት ተከታዮች በየእለቱ የሚገጥማቸውን መልካምም ሆነ መጥፎ አጋጣሚ የተለያዩ የተፈጥሮ ክስተቶች ከትውፊታዊ እምነቱ ጋር በማያያዝ ትርጉም ይሰጡታል። ከግለሰቡ ወይም ከቤተሰቡ በላይ ለሆነ ጉዳይ ኤቃ ባለበት ሄደው ማንም ሰው ቢታመም ወደ ህክምና ተቋም ከመሄድ ኤቀትሳን መጠየቅ የተለመደ ነው። እያንዳንዱ ተፈጥሯዊ ክስተት በአጋጣሚ የሚሆን ሳይሆን በሰው ስህተት ወይም በሰው በጎ ስራ የሪዶንቲ ያደረገው እንደሆነ ይታመናል። የሪዶንቲም ለመጥፎ ስራው ካሳ እንዲከሱ በኤቃ በኩል ይነግራቸዋል። በየአመቱ እህል በተለይ ጤፍ ሲደርስ የአዲስ እህል መቅመሻ ከጤፍ በተዘጋጀ መጠጥ እንዲሁም ምግብ ስጋን ጨምሮ በመደገስ ይበላሉ፤ ይጠጣሉ፤ ይገባበዛሉ። የሪዶንቲን ያመሰግናሉ። ኤቀትሳም እንዲሁ ደግሶ ይጋብዛል።

ኤቃን ኤቃ ያደረገው መንፈስ ከአባቱ የወረሰው ነው። ቆሉ ግን መንፈስ መሆኑን እንጂ እንደኤቃ በሰው ወይም በሚታይ ነገር ላይ አርፎ አይታይም። ሁለቱም የየራሳቸውን ግብር ከአማኞቹ በጊዜው ይፈልጋሉ። አማኞችም ለኤቀትሳ ሆነ ለቆሉ ስእለት ይሳላሉ። ከተሳካላቸው ያስገባሉ። ስእለቱን የረሳ ወይም ቸል ብሎ ጉዳዬ ሞልቷል ብሎ የተወ ከፍ ያለ ቅጣት እንደሚደርስበት ይታመናል።

ኤቃም ሆነ ቆሉ እንዳሉ ሆነው የትውፊታዊ እምነት የሚያምኑት በተሰጣቸው የተለየ ስጦታ የየአማኙን ችግር የሚያውቁና የሚፈቱ ገራትሳ፣ ቡርዣትሳ፣ ከራትሳ እና ገራ የሚባሉ ናቸው። እነዚህም በየቤታቸው ሆነው ውሃ አፍሶ በማንበብ፣ ከእርጥብ እንጨት በሰበቃ እሳት በመፍጠር፣ የጎሽ ቆዳ በማየት፣ የተመረጡ እንስሳትን አንጀት አንብበው የትውፊታዊ እምነቱን ተከታዮች ችግር የሚፈቱ መፍትሄ የሚነግሩና የረከሰን የሚያነጹ ናቸው። በአጠቃላይ የፃራ ብሄረሰብ ትውፊታዊ እምነት ከትውልድ ትውልድ በመከወን በመኖር የሚሸጋገር እንጂ በጽሁፍ የሰፈረ ደንብ የለውም።

## ዋቢ ጽሁፎች

Anders, G. 2012. *Cultural Studies on Folk Religion*, in Scandinavia Print: Interface Media as, Oslo.

Awolalu, J. 1976. "What is African traditional religion"? Studies in Comparative Religion, vol. 10, no. 2. Retrieved from: www. studiesincomparativereligion.com

Degh, L. 1972. "*Folk Narrative*", *Folklore and Folklife: An Introduction*; ed. Richard, M. Dorson. Chicago and London: University of Chicago Press, Print.

Federal Democratic Republic of Ethiopia Population Census Commission Central Statistical Agency.2010. 2007 *Population and Housing Census of Ethiopia*, Addis Ababa.

Motz, M. 1998. The Practice of Belief. Journal of American Folklore 111:339-355.

Mullen, P. 2000. *Belief and the American Folk*; the Journal of American Folklore, Vol. 113, No. 448, pp. 119-143.

Workineh Kelbessa, 2015. *Traditional Oromo Attitudes towards the Environment.* Retrievedon November 2, from https://www. Africaportal. Org

ቀነኣ ለሚ። 2010። "የኦሮሞ ሚቶልጂ ይዘታዊ ትንተና"። በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ሂዩማኒቲስ፤ የቋንቋዎች ጥናትና የጋዛጠኝነትና ኮሚዩኒኬሽን ኮሌጅ፤ የአማርኛ ቋንቋ፤ ስነጽሁፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል በፎክሎር ፒ.ኤች.ዲ. ማሟያ የቀረበ ጥናት።

የብሄረሰቦች ምክር ቤት ፕሮፋይል፣ 2002።